# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 230 ሚያዝያ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፡- ገበሀ ገብሬ

## “ሴቶች ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት ትርጉም ያለው ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል”

-ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት ትርጉም ያለው የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ።

በሀገራዊ ምክክሩ የሴቶች ተሳትፎና ሚና ከባለድርሻ አካላት ጋር ሀገር አቀፍ የውይይት መድረክ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ በተገኙበት ትናንት ተካሂዷል። በመድረኩ ላይ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ እንደገለጹት፤ ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት ትርጉም ያለው የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነው። ሴቶች ሀገርና ሕዝብን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ድምጻቸውን ሊያሰሙ ይገባል።

ከሴቶች የተሰወረ ሀገራዊ ጉዳይ የለም፡፡ ከዚህ አኳያ ሴቶች በምክክሩ በንቃት ሊሳተፉ ይገባል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ሀገራዊ ምክክሩ እንደ ሀገር ያለውን ችግር ለመቅረፍ የሚረዳ ነው ብለዋል።

“ሴቶች ለሀገራዊ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ- የደኅንነት ስጋት መንስኤ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ትንታኔ

በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ በፀጥታ መዋቅሩ አማካኝነት በቁጥጥር ስር ሲውል ይስተዋላል፡፡ በየጊዜው በዘመቻም ይሁን በመደበኛ የፀጥታ ማስከበር ሥራ በሚደረጉ ፍተሻዎች ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያዎችን በቁጥጥር ስር የማዋል ተግባር ዛሬም የቀጠለ ነው፡፡ ይህ ቢሆንም ግን፣ ሕገ ወጥ የመሣሪያ ዝውውር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ እንደመጣ ይነገራል፡፡ የመሳሪያ ዝውውሩ መስፋፋት ለሀገር ሰላም ብሎም ለማኅበረሰብ ደኅንነት አስጊ መሆኑ ላይ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ ምሁራን ለሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር መበራከት ምክንያቶችን ይዘረዝራሉ፤ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመግታት መፍትሔ ያሏቸውን ጉዳዮችም ያስረዳሉ።



ሕገ ወጥ የጦር...ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የግል ሴክተሩን በማብቃት ሁለንተናዊ የልማት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል

- በለገሃር የአራት ሺህ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ተጀመረ

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- የግል ሴክተሩን በማብቃት ሁለንተናዊ የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡በለገሃር የአራት ሺህ የ30/70 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ መጀመሩ ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በለገሃር የ30/70 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ማስጀመሪያ መርሀ-ግብር ትናንት ተካሂዷል፡፡ አራት ሺህ የመኖሪያ ቤቶችን ለመገንባት ዝግጅቱን አጠናቅቆ ወደ ሥራ የገባው ጊፍት ሪል እስቴት እንደሆነ ተገልጿል፡፡

የግል ሴክተሩን...ወደ ገጽ 4 ዞሯል





















## ፓርኩ በዘጠኝ ወራት 18 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ተኪ ምርት አምርቷል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት 18 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ተኪ ምርት ማምረቱን የደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ አስታወቀ።

ፓርኩ በዘጠኝ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዜና



አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ

# የአዲስ አበባን

## የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ማጽናትና ማጠናከር የሁልጊዜ ተግባር ሊሆን ይገባል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ማጽናትና ማጠናከር  የሁልጊዜ ተግባር ሊሆን እንደሚገባ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ አስታወቁ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 37ኛው የአፍሪካ ኅብረት መደበኛ የመሪዎች ጉባኤና 44ኛው የአፍሪካ ኅብረት ሥራ አስፈጻሚዎች ጉባኤ በስኬት እንዲጠናቀቅ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ተቋማትና አካላት በሚያዝያ 18 ቀን 2016 ዓ.ም የምስጋናና የእውቅና መርሀ ግብር አካሂዷል፡፡

በመርሀ ግብሩ ማጠቃለያ ላይ ንግግር ያደረጉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ እንደገለጹት፤ ለ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት  የመሪዎች ጉባኤው በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን በመግለጽ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

አዲስ አበባ የላቀች የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ማጽናትና ማጠናከር  የሁልጊዜ ተግባር ሊሆን ይገባል ያሉት ሚኒስትሩ፤ አፍሪካ ኅብረት ጉባኤን ከዓመት ወደ ዓመት በተሻለ መስተንግዶ እንግዶች ተቀብሎ የመሸኘት ልምዱ እየዳበረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስብሰባዎችን በስኬት በማስተናገድ የዳበረው ባህል  ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመልክተው፤ የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ መስተንግዶ በስኬት በማዘጋጀት ያዳበርነውን ልምድ ማጠናከር ብቻ ሳይሆን፤ አዲስ አበባ የላቀች የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆና እንድትቀጥል የአባቶቻችንን አደራ መወጣት  የሁልጊዜ ተግባራችን ሊሆን ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

ትላልቅ ስብሰባዎችን ማስተናገድ አድካሚ ቢሆንም በሀገር ወዳድ ዜጎችና ተቋማት በስኬት ማጠናቀቅ ተችሏል ያሉት ሚኒስትሩ፤ 37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ የኢትዮጵያን ገጽታ መገንባት ያስቻለ ነበር፡፡ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫነት ኢትዮጵያ ለጥቁር ሕዝቦች ነጻነትና የቅኝ ግዛትን በመታገል ላበረከተችው አስተዋጽኦ የተሰጣት መሆኑንም አስገንዝበዋል፡፡

ጉባኤው ኢትዮጵያ የዓለም የስህበት ማዕከል መሆኗን ያሳየ መሆኑን ገልጸው፤በቀጣይ መሰል ስብሰባዎችን በስኬት በማስተናገድ አዲስ አበባ የስህበት ማዕከልነቷን ማስቀጠል እንደሚገባት ገልጸዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታና የብሔራዊ ኮሚቴ ሰብሳቢ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ በመርሀ ግብሩ የተሠሩ ሥራዎችን አስመልክቶ ባቀረቡት ሪፖርት እንደገለጹት፤ በጉባኤው የተሳተፉ ከተለያዩ ሀገራት የመጡ እንግዶችን በተሳካ መልኩ ተቀብሎ በማስተናገድና በመሸኘት የተሟላ አገልግሎት ለሰጡ ተቋማት ምስጋና አቅርበዋል።

ከእንግዳ አቀባበል እስከ አሸኛኘት ድረስ ከየትኛውም ዓመት የተለየ መስተንግዶ መደረጉን በመግለጽ፤ ለቀጣይ ዓመት የበለጠ የተሻለ አገልግሎት መስጠት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ለጉባኤው መሳካት ብሔራዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ በቅንጅትና በመናበብ መሥራት በመቻሉ ውጤታማ እንደነበርም ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደሯ ማብራሪያ፣ አስፈላጊውን የጸጥታ ሥራ የተሠራ በመሆኑ ያለምንም ችግር  ከ8ሺህ በላይ እንግዶች በሰላም ማስተናገድ ተችሏል፡፡

በሁሉም ዘርፍ ለተመዘገበው ውጤት የአዲስ አበባና የሸገር ከተማ ነዋሪዎች ያደረጉት ትብብር ከፍተኛ መሆኑን በመግለጽ አመስግነዋል፡፡ በጉባኤው መሳካት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላደረጉ ለተቋማትና ግለሰቦች በተለያዩ ደረጃዎች ሰርተፊኬት ተበርክቶላቸዋል፡፡

# “ዕድሎችን ተጠቅሞ በጋራ ለማደግ በፈጠራ ሃሳብ ብቃት ያላቸው ዜጎች በብዛት ያስፈልጉናል”

*- ሙፈሪሃት ካሚል የሥራና ክህሎት ሚኒስትር*

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ዕድሎችን ተጠቅሞ በጋራ ለማደግ በፈጠራ ሃሳብ ብቃት ያላቸው ዜጎች በብዛት ያስፈልጉናል ሲሉ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል ተናገሩ።

በሳይንስ ሙዚየም ሲካሄድ የቆየውና 16 ሺህ ሰዎች የጎበኙት የስታርትአፕ ኢትዮጵያ ኤግዚቢሽን ትናንት ተጠናቋል።

በማጠናቀቂያ መርሀ ግብሩ ንግግር ያደረጉት ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል እንደገለጹት፤ በፈጠራ ሃሳቦች ላይ ተመርኩዘው ችግር ፈቺ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በስፋት የሚያፈልቁ ዜጎችን ማፍራት ይገባል።

በአሁኑ ጊዜ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለቤቶች ያገኙትን ዕድል ተጠቅመው ለሀገር የሚበጅ ሰፊ ሥራ ማከናወን እንዳለባቸው አመላክተው፤ በስታርትአፕ ኤግዚቢሽኑ ላይ የተሳተፉና ዕውቅና ያገኙ ወጣቶች ያገኙትን ዕድል ተጠቅመው ሌሎችን የማብቃት ኃላፊነት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

በተለያዩ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ የቴክኖሎጂና ችግር ፈቺ ፈጠራ ባለቤቶች የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች በማጠናከር በቀጣይ አቅማቸውን ለማጎልበት ሊሠሩ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።



ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ

የስታርትአፕ ኢትዮጵያ ኤግዚቢሽን እንዲካሄድና ዘርፉ እንዲነቃቃ አቅጣጫ በመስጠት ልዩ አስተዋጽኦ ላደረጉት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ ሲሉ ሚኒስትሯ ተናግረዋል።

በተጨማሪም ኤግዚቢሽኑ እንዲሳካ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ተቋማትና ግለሰቦች ምስጋና አቅርበው በስታርትአፕ ውድድር አሸናፊ ለሆኑ የፈጠራ ሃሳብ ባለቤቶች የዕውቅና ሽልማት አበርክተዋል።

ላለፉት አራት ሳምንታት ሲካሄድ በቆየው ኤግዚቢሽን 300 ስታርትአፖች የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ማቅረባቸውን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታውቋል። በተዘጋጀው የአዕምሯዊ ንብረት የፈጠራ ባለቤትነት ውድድር በግብርና ሙያ የአንበጣ መከላከል ሥራ ላይ ትኩረቱን ያደረገው የርጭት መሳሪያ ቴክኖሎጂ ያቀረቡት አቶ ኪዳኔ ገብረስላሴ አንደኛ በመውጣት ልዩ ተሸላሚ ሆነዋል።

በተመሳሳይ በቴክኖሎጂ ፈጠራ ውድድሮች አሸናፊ የሆኑ ቡድኖች ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ዶላር ጀምሮ የተለያዩ ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል።

በመድረኩ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር)፣ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ወልዱ ይመስል እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# በመዲናዋ ደንብ በሚተላለፉ አካላት ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ደንብ በሚተላለፉ አካላት ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

ባለስልጣኑ ከሁሉም ክፍለ ከተማ ከተወጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ባለፉት ዘጠኝ ወራት ባከናወናቸው ሥራዎች ዙሪያ በትናትናው ዕለት ውይይት አካሂዷል።

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በወቅቱ እንደገለጹት፤ መዲናዋ ለነዋሪዎቿ ምቹና ውብ እንዳትሆን ደንብ በሚተላለፉ አካላት ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በቀጣይ በከተማዋ ከተፈቀዱ ቦታዎች ውጪ በዋናና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ላይ የጉልት ንግድ በሚያካሂዱ፣ ተንጠላጣይ የደላላ ማስታወቂያዎችን በሚሰቅሉና ጫማ በሚጠርጉ አካላት ላይ የተጠናከረ እርምጃ እንደሚወሰድ ሻለቃ ዘሪሁን ገልጸዋል፡፡

በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች የግንባታ ዕቃ በሚያስቀምጡ አካላት ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

እንደ ሻለቃ ዘሪሁን ገለጻ፤ በተለይ በከተማዋ በሚገኙ አደባባዮችና መንገዶች ላይ የሚደረጉ ሕገ ወጥ ንግዶች፣ ሕገ ወጥ የቤት ግንባታና መሬት ወረራ ላይ ከሕዝብ ጋር በመተባበር መሥራት በመቻሉ የመዲናዋን ውበት መጠበቅ ተችሏል፡፡

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሁሉም ክፍለ ከተሞች ላይ በተሠራው ሥራ ከ15 ሺህ ኪሎ ግራም በላይ ጤንነቱ ያልተረጋገጠ ስጋ ለሕዝብ ሊቀርብ ሲል መያዙንም ጠቁመዋል፡፡



በተጨማሪም መሬት በሕገ ወጥ መንገድ በግለሰቦች እንዳይወረር በተሰራው ሥራ ከ10 ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ መሬት ወደ ባንክ መግባቱን አስረድተዋል፡፡

የደንብ ማስከበር አባላት የሕዝብን ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ባለስልጣኑ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠቱን ጠቁመዋል፡፡

ሕገ ወጥ የጎዳና ላይ ንግድ ኅብረተሰቡን ለዝርፊያና ለትራፊክ አደጋ እያጋለጠ መሆኑን አውስተው፤ ኅብረተሰብን ያሳተፈ ሥራ በመሠራቱ ጎዳናዎች ነጻ ሆነው እግረኞች በነጻነት እየተንቀሳቀሱ ናቸው ብለዋል፡፡

ሻለቃ ዘሪሁን አክለውም ደንብ መተላለፍን ለመቀነስ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉ ሲሆን፤ የመከላከል ሥራው ውጤታማ መሆኑን አመላክተዋል።

ከደንብ ማስከበር ጋር በተገናኘ ከኅብረተሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የስነ ምግባር ጥሰት በፈጸሙ ደንብ አስከባሪዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል ብለዋል።

ደንብ መተላለፍን የሚጸየፍ ኅብረተሰብ ለመፍጠር ባለስልጣኑ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠቱን ጠቁመው፤ ሁሉም አካላት ትብብራቸውን እንዲያጠናክሩ ሻለቃ ዘሪሁን ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያለው ችግር የሕዝባችንን የለውጥ ተስፋ እንዳያቀጭጭ ማድረግ ይገባል!

በሀገራችን የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት/ የመንግሥት አገልግሎት ከመቶ አስራ አምስት ዓመት በላይ እድሜ ያስቆጠረ ነው። በነዚህ ረጅም ዓመታት የተለያዩ የለውጥ ምዕራፎችን ለማለፍ የተገደደባቸው ሁኔታዎች ቢኖሩም አሁንም አገልግሎቱ በሚጠበቀው መልኩ ውጤታማ መሆን አልቻለም።

በአንድ በኩል በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት፤ ከዚያም ባለፈ ሲቪል ሰርቪሱ ከፖለቲካ ነፃ ሆኖ ሥራዎችን የሚያከናውንባቸው የተመቻቸ ሁኔታ አለመኖር፤ ተጠያቂነት የሰፈነበት፣ ቀልጣፋ እና ዘመናዊ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ እውን እንዳይሆን ዋነኛ ተግዳሮት ሆኗል።

በተለያዩ ወቅቶች ሲቪል ሰርቪሱን ለማሻሻል/ዘመኑን እንዲዋጅ የተደረጉ ጥረቶችም ቢሆኑ በወቅታዊ ሀገራዊ ፖለቲካ ተጠልፈው፤ በመሠረታዊነት የተነሱበትን ዓላማ ሳያሳኩ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለውም ለአገልግሎቱ ተጨማሪ ፈተና ሆነው አልፈዋል። ሀገርንም ለብዙ ብክነት ዳርገዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ብዙ ጫና ተደርጎባቸው፤ ከፍተኛ ሀብት የፈሰሰባቸው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ሳይቀሩ ከፍ ባለ ሞቅታ እና መጯጯህ ቢጀመሩም፤ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ተጨማሪ ግርግር እና አለመረጋጋት ከመፍጠር ባለፈ ይህ ነው የሚባል ትርጉም ያለው ውጤት ማስመዝገብ አልቻሉም።

ብዙ እንደ ተባለላቸው፤ እንደ ተዘመረላቸው ሳይሆን የአንድ ወቅት ጩኸት ሆነው፤ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የሚፈለገውን ለውጥ ሳያስገኙ አሳዛኝ ትዝታዎችን ጥለው አልፈዋል። በአገልግሎቱ ውስጥ የነበሩ ችግሮች ለዘለቄታው ከመፍታት ይልቅ የበለጠ የሚገነግኑበትን ሁኔታ ፈጥረው አልፈዋል።

ከዚህ የተነሳም ከመቶ አስራ አምስት ዓመት በላይ እድሜ ያለው የሀገራችን የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት ራሱን በሁለንተናዊ መንገድ አዘምኖ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ሳይችል ቀርቷል። በዚህም ዛሬም አገልግሎቱ የሕዝባችን ዋንኛ የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ ነው።

በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያለውን ይህን የገነነ ችግር ለመፍታት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። አገልግሎቱ በተሻለ ሥርዓት፣ እውቀት፣ ክህሎት እና የሕግ አግባብ የሚመራበትን፣ በቴክኖሎጂ እየታገዘ ዘመኑን እንዲዋጅ ለማድረግ ረጅም ርቀት ተኬዷል። በዚህም ተስፋ ሰጭ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

ይህም ሆኖ ግን እንደ ሀገር ገብተንበት ከነበረው አስቸጋሪ ፈተና ጋር በተያያዘ አገልግሎቱን ቀልጣፋ እና ዘመናዊ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ መሆን ሳይችሉ ቀርተዋል። እንዲያውም ተጨማሪ የችግር ምንጭ በመሆን ለውጡን ክፉኛ ሲፈታተኑ ታይተዋል።

በዚህ የለውጥ ወቅት፣ በሀገሪቱ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት ውስጥ ኃላፊው ቢሮ የለም፣ መመሪያው አይፈቅድም፣ ሲስተም የለም፤ ወዘተ የሚሉ የተለመዱ ከትናንት ያልተሻገርናቸው ችግሮች አሉ፤ የአገልግሎት ፈላጊዎች ከበሬታ መንፈግ፣ ረጅም ሰልፍ፤ ያልተገባ እንግልት ብዙ ቦታ የሚስተዋሉ ናቸው።

በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም መመሪያ ባለመኖሩም፤ በመንግሥት የሥራ ሰዓት ባለጉዳይ ጉዳዩን የሚፈጽምለት እጥቶ ረጂሙን የመንግሥት የሥራ ሰዓት በሶሻል ሚዲል ሚዲያ ውስጥ የሚያሳልፉ የመንግሥት ሠራተኞች ቁጥር ቀላል አይደለም። እነዚህን ሠራተኞች ለአገልግሎቱ ተጨማሪ ፈተና ሆነዋል።

ሕጋዊ የቢሮ አገልግሎቶችን በእጅ መንሻ፤ ከዛም ባለፈ አስገዳጅ በሆነ ድርድር ለመፈጸም ወደ ቢሮ የሚገቡ፣ ሌብነትን ዋነኛ የቢሮ ሥራቸው አድርገው የሚንቀሳቀሱ የመንግሥት ሠራተኞችን በስፋት እንደሚታዩም ተገልጋዩ እያነሳ ነው።

ችግሮቹ አሁን ላይ መላው ሕዝባችን በብዙ ተስፋ እና መስዋዕትነት የጀመረውን ለውጥ በከፍተኛ ሁኔታ እየተፈታተነ ነው። ፈጣን እና የማያዳግም ርምጃ ካልተወሰደበት፣ ለውጡን የበለጠ ስጋት ውስጥ በመጨመር ከቀደሙት ጊዜያት በከፋ መልኩ ተጨማሪ የአደጋ ምንጭ መሆኑ የማይቀር ነው።

መንግሥት ይህንን ከትናንት የተሻገረ ዛሬ ላይ ሀገር እና ሕዝብን ብዙ ዋጋ እያስከፈለ ያለ ሀገራዊ ችግር ለመፍታት የጀመራቸውን የለውጥ እንቅስቃሴዎች በላቀ ዲሲፕሊን ሊመራ ይገባል። ለእያንዳንዱ ችግር የማያዳግም ርምጃ በመውሰድ ችግሩ የሕዝባችንን የለውጥ ተስፋ እንዳያቀጭጭ ማድረግ ይጠበቅበታል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓቱ ሊፈተሽ ይገባል!

**ጋሹ ይግዛው (ከወሎ ሠፈር)**

በአሁኑ ጊዜ የትራንስፖርት ታሪፉን የሚወሰነው የመንግሥት አካላት ናቸው? ወይስ ተራ አስከባሪዎች? የሚለው ጥያቄ ሁሌ በጭንቅላቴ ይመላለሳል። ይህን የምልበት ምክንያት ጨለምተኛ ሆኜ ወይም ሰዎችን የመኮነን አባዜ ኖሮኝ ሳይሆን በየታክሲ ተራውና በየመኪና መናኸሪያው ለተጓዦች ታሪፉን አስቀድመው የሚናገሯቸው ተራ አስከባሪዎች በመሆናቸው ነው፤ የትራንስፖርት ታሪፍ የሚወሰነው በመንግሥት አካላት ነው? ወይስ በተራ አስከባሪዎች ነው? የሚለው ጥያቄ በአዕምሮዬ እንዲመላለስ ያደረገው።

ድንገት ደፍረው ለምን? የሚሉ ተሳፋሪዎች ካሉ "ካልተስማማህ መውረድ ትችላለህ" ("ካልተስማማሽ መውረድ ትችያለሽ") የሚለው መልሳቸውም ሁልጊዜ ተሳፋሪዎችን የሚያሸማቅቅ ነው። የሚገርመው ለምን? ያለው ተሳፋሪ የግልምጫና የስድብ ውርጅብኝ የሚጎርፍበት በሹፌሮች፣ በረዳቶችና በተራ አስከባሪዎች ብቻ እንዳይመስላችሁ፤ ከሌሎች ተሳፋሪዎችም ጭምር ነው።

ድሮ የአጭር ርቀት ታሪፍ 35 ሣንቲም፣ የረጅም ርቀት ታሪፍ 70 ሣንቲምና ከዚያ በላይ በነበረበት ጊዜ ለታክሲ ረዳቶቹ 40 ሣንቲም ወይም 50 ሳንቲም ወይም አንድ ብር ከተሰጣቸው 05፣ 15 እና 30 ሳንቲሞችን አስበው ነበር የሚመልሱት። ካልመለሱም ከተሳፋሪው የመልሱልኝ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል።

አሁን አሁን ደግሞ በተቃራኒው በመንግሥት የተወሰነው ታሪፍ 5 ብር፣ 7ብር ከ50 ሣንቲም፣ 10 ብር እና 15 ብር ቢሆንም እንኳን በተራ አስከባሪዎቹ እና በታክሲ ረዳቶቹ ውሳኔ ከ5 ብር እስከ 7 ብር ከ50 ሣንቲም ላለው ታሪፍ የትም ቢሆን የሚከፈለው 10 ብር ነው ወይም 15 ብር ነው ስለሚባሉ መልስ ይሰጠኝ ብሎ የሚጠየቅ ተሳፋሪ የለም። ከጠየቀም የስድብ ናዳ ይወርድበታል፤ ወይም አሽሟጣጭ ይበዛበታል። የ5 ብር ታሪፍ የትም 10 ብር ነው፤ የ10 ብሩ ታሪፍ የትም 20 ብር ነው፤ የ15 ብሩ ታሪፍ የትም 30 ብር ነው በሚል እጥፍ አስከፍሎ መጫን እየተለመደ መምጣቱን ታዝባችሁ ታውቃላችሁ?

ተሳፋሪዎች አቤት ቢሉም አብዛኛውን ጊዜ ሰሚ ስለማያገኙ የተጠየቁትን ከፍለው ከመጓዝ ውጭ ምርጫ የላቸውም። በመንግሥት የተወሰነው ታሪፍ 5 ብር፣ 7ብር ከ50 ሣንቲም፣ ወይም 12 ብር ቢሆንም 2 ብር ከ50 ሣንቲም፣ 3 ብር እና 5 ብር መመለስ ክልክል እስኪመስል ድረስ መልስ የሚሰጡ ረዳቶች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ቢባል ማጋነን አይመስለኝም።

የትራንስፖርት ታሪፍን የመንግሥት አካል የማይቆጣጠረው እስከማይመስል ድረስ ከብዙሃን ትራንስፖርት (አንበሳና ሸገር አውቶብሶች) በስተቀር አብዛኞቹ ታክሲዎችና በተለምዶ ሚኒባስ የሚባሉት ወደ መካከለኛ ርቀት የሚሄዱ መኪኖችም መንግሥት ባወጣው ታሪፍ ሳይሆን እነሱ ባወጡት ታሪፍ ነው የሚጭኑት።

የሚገርመው ደግሞ ከታሪፍ በላይ አስከፍለውም ጠጋ ጠጋ በሉ ማለትም የማይቀር ነው። አሁን አሁን አንዳንድ የብዙሃን ትራንስፖርትም (አንበሳና ሸገር አውቶብሶች) ረዳቶች ማለቴ ነው፤ አንዳንዴ መልስ የለኝም ስለሚሉ ተሳፋሪው መውረጃው ሲደርስ ጥሎላቸው ስለሚወርድ ይችን ዘዴ መጠቀም ጀምረዋል።

ጠጋ በሉ ወይም ይህን ያህል ክፈሉ ሲባሉ ለምን ብለው የሚጠይቁ ተሳፋሪዎች ካሉም ገብጋባ፤ ድሃ ከሚለው አሽሟቃቂ ስድብ በላይ "ካልተስማማህ ውረድ" ("ካልተስማማሽ ውረጅ") የሚል ማስጠንቀቂያ ስለሚከተላቸው ደፍሮ የሚከራከር ተሳፋሪም አይኖርም።

የሚገርመው ጠጋ በል ሲባል አልጠጋም የሚል ተሳፋሪ ካለም እንደሙብት ስለሚቆጠር ግልምጫና የስድብ ውርጅብኝ የሚደርስበት ከተራ አስከባሪዎች፣ ከረዳቶችና ከሹፌሮች ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተሳፋሪዎችም ጭምርም መሆኑ ነው። ከተሳፋሪዎቹ መካከልም እባካችሁ በሠላም እንሂድበት የሚለው ተስፋ አስቆራጭ ንግግርም ለረዳቶቹና አሽከርካሪዎቹ የልብ ልብ የሰጣቸው ይመስላል።

ይህን የምለው ሕግ ጠብቀው የሚያስከፍሉ መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ረዳቶችና በአግባቡ የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች መኖራቸውንም ሳልዘነጋ ነው። ፀሐይ እያቃጠላቸው፤ ዶፍ እየወረደባቸው፣ ውርጭና ብርዱ እያንገበገባቸው በየመንገዱ ቆመው በአግባቡ የሚቆጣጠሩ የትራፊክ ፖሊሶችና የመንገድ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችም የሚዘነጉ አይደሉም።

ተሳፋሪዎች የታሪፉን ዋጋ ካወቁ ለምን ብለው መጠየቅ እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው። አለበለዚያ መንግሥት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪና አሽከርካሪ የትራፊክ ፖሊስ ወይም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ማቆም እንደማይችልም መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል።

ለዛሬ የራሴን ገጠመኖች ላውጋችሁ። አንዴ ከአውቶቡስ ተራ ወደ ቦሌ ማተሚያ ተሳፍሮ ሲሄድ የነበረ አንድ ተሳፋሪ ታሪፉ 5 ብር መሆኑን ስለሚያውቅ 10 ብር ሰጥቶ የትም 10 ብር ነው በሚል ሰበብ መልስ አልሰጠው ከሚለው ረዳት ጋር እየተጨቃጨቁ ሲጓዙ ተሳፋሪው የትራፊክ ፖሊስ አይቶ ለመንገር አንገቱን በመስኮት ብቅ ሲያደርግ 5 ብሩን ተጣድፎ የመለሰለትን አጋጣሚ አልረሳውም።

ሌላ ጊዜ ደግሞ ከቦሌ ማተሚያ እስከ ተክለሃይማኖት መንግሥት ያወጣው ታሪፍ 7ብር ከ50 ሣንቲም ቢሆንም ተሳፋሪዎች ጭቅጭቁ ስለሰለቻቸው 10 ብር እየከፈሉ ለመጓዝ እየተገደዱ ያሉበት ሁኔታ አሁንም አልተለወጠም። ያን ቀን አንድ ተሳፋሪ ከሁለት ልጆቹ ጋር ሲጓዝ 50 ብር ሰጥቶ 20 ብር ይመልስልኛል ብሎ ሲጠብቅ 5 ብር ብቻ ስለተመለሰለት ለምን ብሎ ሲጠይቅ ለአንድ ሰው 15 ብር ነው አለው ረዳቱ።

አላግባብ ከታሪፍ ውጭ ስላስከፈልከኝ የትራፊክ ፖሊስ ካየሁ ግን ስንት እንደከፈልኩ እናገራለሁ አለና ጉዟችን ቀጥለን እያለ ረዳቱ ቀድሞ የትራፊክ ፖሊስ ስላዬ የተሰጠውን 5 ብር ተቀብሎ 20 ብር ሲመልስለት በድርጊቱ ተፀፅቶ መስሎን ነበር። ነገር ግን 20 ብሩን የመለሰለት የትራፊክ ፖሊስ ስላዬ መሆኑን ሳይ በጣም አዘንኩ። እስከ መቼ ነው የሌባና ፖሊስ ጨዋታ የሚጫወቱት የሚለውም አሳሰበኝ።

እንዲሁ በተመሳሳይ ከአምቦ ወደ አዲስ አበባ ስንመጣም አንድ ተሳፋሪ በታሪፉ መሠረት ሂሳብ ሲሰጠው ረዳቱ ያስጨምራል አለው። ተሳፋሪውም ታሪፉን ስለሚያውቅ የታሪፉን ዝርዝር አሳየኝና

ወደ 5ኛው ገጽ ዞሯል

ዜና

# "ሴቶች ለሀገራዊ ምክክሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደሀገር መነጋገርና ምክክርን አማራጭ ማድረግ እንደሚገባ አስገንዝበው፤ ሴቶች ለሀገር መፍትሔ ፍለጋ ላይ ጉልህ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል።

ሴቶች ሀገራዊ ወሳኔ በሚሰጥባቸው ሂደቶች ላይ በመገኘት በንቃት ሊሳተፉ እንደሚገባ የገለጹት ፕሬዚዳንቷ፤ ችግሮችን ለመፍታት ከምክክር ሌላ መፍትሔ እንደሌለም አመልክተዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ እንደ ሀገር ያለውን ችግር ለመቅረፍ የሚረዳ ሂደት መሆኑን የገለጹት ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ፤ጥልን፣ ኩርፊያና ማግለልን በማራቅ ችግሮች ለመፍታትም ምክክርን አማራጭ ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በግጭቶች ሳቢያ መከራ የሚፈራረቅባቸው ሴቶች መሆናቸውን በመግለጽ፤ ሴቶች ሀገራዊ ወሳኔ በሚሰጥባቸው ሂደቶች ላይ በመገኘት በንቃት ሊሳተፉ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ሀገራዊ ምክክሩ እውን እንዲሆን ትርጉም ያለው የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነው ብለዋል።

በሀገሪቱ ሴቶች ከ50 በመቶ በላይ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

ሴቶች ከቤተሰብ እስከ ሀገር የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም ያሉት ዶክተር ኤርጎጌ፤ በምክክሩ በንቃት በመሳተፍ የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ እንደሚገባም ተናግረዋል።

የሀገራዊ ምክክሩ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ፣ በኮሚሽኑ አካታችና ሁሉን አቀፍ ምክክር ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ኮሚሽኑ ሴቶች ተጨባጭ በሆነ መልኩ እንዲወከሉ እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ ሴቶች ለምክክሩ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ከፍተኛ መደላድል መፈጠሩን ገልጸዋል።

ሴቶች በምክክሩ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማንቃት እንደሚያስፈልግ የገለጹት ዋና ኮሚሽነሩ፤ ሴቶች በሀገራቸው ጉዳይ ያገባናል ብለው የሂደቱ አካል ሊሆኑ ይገባል ብለዋል። ሴቶች ቁልፍ ተዋንያን የሆኑበት ሀገራዊ ምክክር ለማካሄድ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ እንደሚገባ አስረድተዋል።

# ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ- የደኅንነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የሰላምና ደህንነት መምህሩ ዶ/ር ተመስገን ቶማስ፣ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር ለሀገር ሰላም ማጣት ትልቁ መንስዔ ነው ይላሉ፡፡ የጦር መሳሪያ ፍላጎት ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እንዲጨምር ዋነኛው ምክንያት እንደሆነም ያነሳሉ፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፣ የአፍሪካ ቀንድ ተብሎ በሚጠራው የአህጉሪቱ ክፍል በሚገኙ ሀገራት የሚከሰቱ፣ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ያሉ ግጭቶች ለጦር መሳሪያ ፍላጎት መጨመር ምክንያት ሆነው ይጠቀሳሉ፡፡

ዶክተር ተመስገን እንደሚሉት በፖለቲካም ሆነ በአካባቢያዊ አጀንዳ ነፍጥ ያነገቡ እና ጦርነትን አማራጭ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ኢ -መደበኛ አደረጃጀቶች ሁሉ የጦር መሳሪያ ፍላጎት ይኖራቸዋል፡፡ የጦር መሳሪያ ፍላጎት ሲኖር መሳሪያ ሸጦ ትርፍ ማጋበስ የሚፈልግ ይፈጠራል፡፡ የጦር መሳሪያ ፈላጊና አቅራቢ ሲገናኙ የጦር መሳሪያ ልክ እንደ ሌሎች መደበኛ የግብይት እቃዎች ሁሉ በግብይት ሥርዓት ውስጥ ይገባል፤ የጦር መሳሪያ ደግሞ፣ የፈለገ አካል ሁሉ የግሉ ሊያደርገው የሚገባ አይደለም፡፡

ይህን ችግር ለመቅረፍ የጦር መሣሪያ ፈላጊ፣ ደላላና አቅራቢ ሰንሰለትን መበጠስ ያስፈልጋልም የሚሉት ዶክተር ተመስገን፤ ለዚህም ጠንካራ መዋቅራዊ ሥርዓት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ይህ ልውውጥ ከየት መስመር ነው የሚመጣው የሚለውን የግንባር ላይ ቁጥጥር ማጠናከር እና በዚህ ሥራ ላይ የተሰማሩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያስችላቸውን ተቋማዊ ጥንካሬ መፍጠር ይገባል። ሕገ ወጥ መሳሪያ ዝውውር ላይ በሚሳተፉ አካላትም ላይ እንዲሁ ጠንከር ያለና አስተማሪ እርምጃ መውሰድም ያስፈልጋል፡፡

ዶክተር ተመስገን ከጠቀሷቸው መፍትሔዎች በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ የመሳሪያ ፍላጎት እንዲቀንስ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖረውም ያስረዳሉ፡፡ እንደ እርሳቸው ሃሳብ፣ ፖለቲካዊ ለሆኑ ችግሮች ፖለቲካዊ መፍትሔ እየተሰጣቸው ሲሄዱ ግለሰቦችና ቡድኖች ለመሳሪያ ያላቸው ፍላጎት እየቀነሰ ይሄዳል፤ በተመሳሳይም ሁከት፣ ጽንፈኝነት፣ ግጭቶች እየቀነሱ ይሄዳሉ፡፡

ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር ፍላጎት እርስ በእርስ የሚታኮስ ቡድን ስላለ ብቻ የሚጨምር አይደለም ያሉት ዶ/ር ተመስገን፤ ዜጎች የደህንነት ስጋት ሲሰማቸውም ጭምር ራሳቸውን ለመጠበቅ ህጋዊ ባልሆነ መልኩ መሳሪያን መታጠቅ ምርጫቸው ያደርጋሉ ብለዋል፡፡ መንግሥት ዜጎች የሚተማመኑበት የሕዝብን ደህንነት መጠበቅ የሚችል ከሆነ የግለሰቦች መሳሪያን የመታጠቅ ፍላጎትን በከፍተኛ መጠን መቀነስ እንደሚያስችለው ገልጸዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ዶ/ር ደጉ አስረስ በበኩላቸው እንደሚሉት፣ አንድ መንግሥት ሲቋቋም ከሌሎች አደረጃጀቶች ለየት የሚያደርገው መሳሪያን በቁጥጥሩ ስር ማዋል መቻሉ ነው፡፡ የመሳሪያ ዝውውር፣ ትጥቅ እና መሳሪያን ጥቅም ላይ የማዋል ተግባር በመንግሥት ቁጥጥር ስር ካልዋለ የሀገርን ሰላም በዘላቂነት ለማስፈን በሚደረገው ጥረት እንቅፋት ከመሆኑም ባሻገር፣ የመንግሥት ህልውናም ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል ይላሉ፡፡

እንደ ዶ/ር ደጉ ማብራሪያ፣ ከመንግሥት ኃይል ውጪ ያለ አካል መሳሪያ ሲይዝ ወንጀሎች ይበራከታሉ፣ መንግሥትም ዜጎቹን የመጠበቅ አቅሙ ይዳከማል፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉ አደረጃጀቶችም ዋስትና መስጠት አይችልም፡፡ መንግሥት ይህንን መከላከል የሚችል ጠንካራ ሥርዓት ሲኖረው የመሳሪያ ዝውውሩን መግታት ብሎም ጠንካራ አገልግሎት ለሕዝቡ መስጠት ያስችለዋል፡፡

ጠንካራ የሚባሉ ሀገራት ጥንካሬያቸው የሚለካው በቀዳሚነት መሳሪያን በማምረት ሁለተኛው ደግሞ ያመረቱትን መሳሪያ በመቆጣጠር ነው ያሉት ዶ/ር ደጉ፣ በእነዚህ ሀገራትም ቢሆን አልፎ አልፎ ችግሮች ባይጠፉም መሳሪያን መቆጣጠር ካልቻሉ ሀገራት የተሻለ ሰላም የሰፈነባቸው ሊሆኑ እንደማይችሉ ይጠቅሳሉ፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶ/ር መብራቱ አለሙ ደግሞ መሳሪያን ሕጋዊ ማድረጉ በራሱ በሚገባ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ እንደ እርሳቸው እይታ፣ ከፀጥታ አካላት (ከሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት፣ ፖሊስ፣ የመንግሥት ኃላፊዎች አጃቢዎች)፣ ከፍተኛ የሀብት መጠን ካላቸው ባለሀብቶች ውጪ መሳሪያ በማንም ሰው እጅ መግባት የለበትም፡፡ በግለሰቦች ዘንድ መሳሪያን በቀላሉ ሕጋዊ የማድረጉ ልምድ መገታት አለበት፡፡ ይህን ልምድ ከማስቀረትም ባሻገር መንግሥት በማኅበረሰቡ ውስጥ ተበትነው የሚገኙ መሳሪያዎች የመሰብሰብ ሥራ መስራት አለበት፡፡

በሀገራችን ያለው ግጭት እንዲባባስ ከሚያደርጉ ሰበቦች መካከል አንደኛው የሕገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውር እንደሆነ ያነሱት ዶ/ር መብራቱ፣ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት በተለይ ከኬንያና ሱዳን ጋር ረጅም ድንበር የምትዋሰን መሆኗን ጠቅሰው፣ ከጎረቤት ሀገራት ወደ ሀገራችን የጦር መሳሪያ ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ እንደሚገባ ያነሳሉ፡፡

ዶ/ር መብራቱ ወደ መፍትሔው ሲሻገሩ በዋናነት ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ጠንካራ መሆን እንደሚገባውም አስተያየት ይሰጣሉ፡፡

የፀጥታ አካላት ሕገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውርን ለመቅረፍ የሚያስችሉና አቅምን ለማጎልበት የሚጠቅሙ ልምዶችና ቴክኖሎጂዎችን ከሌሎች ሀገራት እንዲወስዱ ቢደረግ መልካም እንደሆነም ይመክራሉ፡፡

ኅብረተሰቡን የሀገር ሰላም ግንባታው አካል በማድረግ ሕገ ወጥ የመሳሪያ ንግድ ላይ የተሰማሩ አካላትን ሲመለከት እንዲጠቁም ማድረግ፤ ጥቆማ ለሚሰጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች መንግሥት የሕግ ከለላና ማበረታቻ ቢሰጥ ሕገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውርን መግታት ይቻላል የሚል አስተያየትም ሰጥተዋል፡፡

# የግል ሴክተሩን በማብቃት ሁለንተናዊ የልማት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ግንባታውን ባስጀመሩበት ወቅት እንደገለጹት፤የግል ሴክተሩን በማብቃት ሁለንተናዊ የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

የግል ሴክተሩን በማብቃትና የመሪነት ሚናውን በማሳደግ ያለውን እድል ወደ ልማት መቀየር ወሳኝ ነው ያሉት ወይዘሮ አዳነች፤በመኖሪያ ቤቶች ላይ የተጀመረው የመንግሥትና የግል አጋርነት የልማት ፕሮጀክት ለዚህ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ በከተማው ያለውን ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቅረፍ ባደረገው ጥረት በርካታ ቤቶች ገንብቶ ለተጠቃሚው ማስረከብ ችሏልም ብለዋል።

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፤ በከተማው የመኖሪያ ቤት እጥረት ሙሉ በሙሉ መቅረፍ በመንግሥት ጥረት ብቻ የማይቻል በመሆኑ ከተማ አስተዳደሩ ለቤት ግንባታ የሚሆኑ ግብዓት በማሟላትና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ከግል አጋር ድርጅቶች ጋር እየሠራ ይገኛል።

ግንባታው በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ የድጋፍና የክትትል ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ከንቲባ አዳነች አመልክተው፤ በቀጣይም የከተማዋን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ለማጣጣም በግል አልሚዎች፣ በማህበር፣ በሪል እስቴት እንዲሁም በተለያዩ አማራጮ እንዲለማ ትኩረት መደረጉን አብራርተዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በዘርፉ የግል ሴክተሩ የበለጠ እንዲጠናከር የሚያስችል ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ በከተማው የቤት ችግር ለመቅረፍም ከሌሎች የመኖሪያ ቤት አልሚ ድርጅቶች ጋር እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የጊፍት ሪል እስቴት ማህበር መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ገብረኢየሱስ ኢጋታ በበኩላቸው፤ የግል ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር በጋራ መሥራት መቻላቸው በከተማው ያለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ከማቃለሉ ጎን ለጎን ጥራቱን የጠበቀና ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ያለው የመኖሪያ መንደር ለመገንባት ያግዛል ብለዋል፡፡

በፕሮጀክቱ በመጀመሪያው ዙር አራት ሺህ ቤቶች የሚገነቡ ይሆናል ያሉ ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አቶ ገብረ ኢየሱስ አክለውም፤ የመኖሪያ መንደር ከፍታቸው ከ14 እስከ 22 የሚሆኑ ፎቆች የሚኖሩት ሲሆን፤ የመጀመሪያው ዙር ግንባታ እንደተጋመሰ በሁለተኛ ዙር ለሚገነቡ ተጨማሪ 8 ሺህ ቤቶችና የንግድ ማዕከላት ጊፍት ሪል እስቴት ከእህት ኩባንያዎቹና ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ አጋሮቹ ጋር በዲዛይን፤ ቴክኖሎጂና ፋይናንስ የቅድመ ዝግጅት ሥራ በመስራት ላይ ይገኛል ነው ያሉት፡፡

እንደ አቶ ገብረኢየሱስ ገለጻ፤ የለገሃር የመኖሪያ መንደር ፕሮጀክት በላቀ ጥራትና ዘመኑን በዋጀ የቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚገነቡ 3 ሺህ 540 የመኖሪያ ቤቶች 460 የሱቅ፣ ይገነባሉ፡፡ ግንባታው ትምህርት ቤትና ሌሎች ማህበራዊ መገልገያዎችን የሚያካትት ይሆናል ያሉ ሲሆን ፤ በስምንት ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# ፓርኩ በዘጠኝ ወራት 18 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ የሺጥላ ሙሉጌታ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በፓርኩ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሀብቶች በአልባሳትና ጨርቃ ጨርቅ፣ በብቅል እንዲሁም በሌሎች የኢንቨስትመንት አማራጮች ተሰማርተው ተኪ ምርቶች እያመረቱ ይገኛሉ።

ፓርኩ በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት 18 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ተኪ ምርት አምርቷል ያሉት አቶ የሺጥላ፤ በዚህም አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ የገበያ ትስስሮች ተፈጥሯል። ይህም በዋናነት የቢራ ገብስ አምርቶ ለኩባንያዎች በማቅረብ የተፈጠረ ነው ብለዋል።

ፓርኩ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ወደ ውጭ ከላካቸው ምርቶች ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት ችሏል ያሉት አቶ የሺጥላ፤ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ ተኪ ምርት በማምረትና በገበያ ትስስር ውጤታማ ተግባራት ተከናውነዋል። በዚህም ለ335 የሚሆኑ ዜጎች የእውቀት ሽግግር መፈጠሩን ገልጸዋል።

ፓርኩ ከሁለት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሠራተኞች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ተጠቃሚ አድርጓል። ከዚህም ባለፈ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በየወሩ ከ400 ሺህ ብር በላይ ለአካባቢው ማህበረሰብ ወጪ ያደርጋል ያሉት አቶ የሺጥላ፤ ይህም ድጋፍም ለአካባቢው አረንጓዴ ልማት እና ሥራ እድል ፈጠራ የሚውል መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ የሺጥላ ገለፃ፤ አማራ ክልል ከሚገኙ የኢንዱስትሪ ልማት ፓርኮች መካከል ደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ አንዱ ነው። ከአዲስ አበባ በ130 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በ100 ሄክታር መሬት ላይ የተገነባ ነው። በዚህም ስምንት ዋና ዋና የፋብሪካ ሼዶችን ይዟል። የማምረቻ ሼዶቹ አምስት ሺህ 500 ካሬ ሜትር ስፋት ያላቸው ናቸው።

ለኢንዱስትሪ ፓርኩ የውሃ፣ የመብራት፣ የቴሌኮም አገልግሎትና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመርና አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች ተሟልተዋል ያሉት አቶ የሺጥላ፤ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ወደ ሥራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን በማቃለል ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በፓርኩ ውስጥ የጉምሩክ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በአንድ ማዕከል አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ይህም ለባለሀብቶች መልካም የሥራ ከባቢን ፈጥሯል ብለዋል።

ኢንዱስትሪ ፓርኩ በ2015 በጀት ዓመት ለሦስት ሺህ 568 ዜጎች አዳዲስ የሥራ እድል ፈጥሯል። በፓርኩ ውስጥ የሚሠሩ ኩባንያዎችም ከ100 ሺ በላይ ከሚሆኑ የአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ የገበያ ትስስር መፍጠራቸው ተመልክቷል።

# የትራንስፖርት አገልግሎት...

ከ3ኛው ገጽ የዞረ

እጨምራለሁ እንጂ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ አልከፍልም ስላለው አዲስ አበባ ሲደርስ ሂሳብ የተቀበለበትን አጋጣሚ አስታውሳለሁ።

እያንዳንዱ ተሳፋሪ መብቱን ማስጠበቅ ያለበት ራሱ ነው። መንግሥት በእያንዳንዱ መኪና የትራፊክ ፖሊስና የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ማቆም ስለማይችል መንግሥትን ብቻ ማማረርም ተገቢ አይመስለኝም። ይልቅስ እያንዳንዱ ተሳፋሪ ተባብሮ ሕገ ወጦችን መከላከል ይጠበቅበታል።

አንዱ ለትራፊክ አደጋ መንስኤ የሚሆነውም መኪናዎቹ ከአቅማቸው በላይ ስለሚጭኑ ይመስለኛል። የሚመለከተው አካልም ሁኔታው መኪናዎቹ በአቅማቸው ልክ እንዲጭኑ ለማድረግ ቁጥጥሩን ጠበቅ ማድረግ አለበት ።

በርግጥ ተሳፋሪዎች ለምን ጠጋ በሉ እንባላለን፤ ለምንስ ከታሪፍ በላይ እንጠየቃለን ብለው የማይከራከሩትም አብዛኛውን ጊዜ ሰሚ ስለሚያጡ መፍትሔ ለሌለው ነገር መጨቃጨቅ ሰልችቷቸው እንደሆነ ለመገመት ብዙም የሚቸግር አይደለም ፤ ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት የሚመለከተው አካል መፍትሔ የመስጠት ግዴታ ያለበት ይመስለኛል።

በተለይ በሥራ ጉዳይ በአንድ መስመር በተከታታይ የሚመላለሱ ተሳፋሪዎች ሁሉም አሽከርካሪዎችና ረዳቶች አድመው ስለማይጭኗቸው እና ከሥራቸው ቢቀሩ ወይም ቢያረፍዱ የሚገጥማቸውን ችግር ስለሚያውቁ ከሥራ ከመቅረትና አርፍዶ ከመግባት ተጠጋግቶ ከመቀመጥና የጠየቁትን ከፍሎ ከመሄድ ውጭ ምርጫ የላቸውም።

አንዳንድ የታክሲ ተራ አስከባሪዎች እና ረዳቶችም መብታቸው እስኪመስል ድረስ ተሳፋሪዎችን ያመናጭቃሉ፤ ሲያሻቸውም ይሳደባሉ። ለዚህ ጋጣወጥ ባሕሪያቸው ሀይ የሚላቸው አካል ሊኖር ይገባል። ችግሩ የሚፈጠረው ሀይ የሚል የመንግሥት አካል በመታጣቱ ስለሆነ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እየተከታተሉ የማስተካከል ግዴታ አለባቸው።

ተሳፋሪዎችም ጠጋ በሉ ሲባሉ እና ከታሪፍ በላይ ሲጠየቁ በኅብረት ለምን ብለው መጠየቅ ይኖርባቸዋል። አለበለዚያ መንግሥት ለእያንዳንዱ መኪና የትራፊክ ፖሊስ ወይም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ማቆም ስለማይችል ለሁሉም ነገር መንግሥትን ተጠያቂ ማድረግ ተገቢ አይመስለኝም። የመኪናዎች ባለቤቶችም ቢሆኑ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ሲያወጡ ሕዝብን በአግባቡ ለማገልገል መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም።

ከከተማ ውጭ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ በተለምዶ ሚኒባስ የሚባሉት መኪና አሽከርካሪዎችና ረዳቶች መኪናቸውን አቁመው የሚጠፉት ደግሞ ከተወሰነ ሰዓት በኋላ ታሪፍ ጨምረው ለመጫን ነው፤ ተሳፋሪውም ስለሚጨንቀው የጠየቁትን ከፍሎ ይሄዳል።

አሁን አሁን ተሳፋሪዎች የግድ እየሆነባቸው እንጂ መንገድ ባይሄዱ ይመርጣሉ። ምክንያቱም በአንድ በኩል ተሳፋሪው በእጁ ከያዘው ገንዘብ በላይ ስለሚጠየቅ የያዝኩት ገንዘብ ባይበቃኝስ ምን እሆናለሁ? በሚል ስጋት፤ በሌላ በኩል መኪናዎቹ ከአቅማቸው በላይ ሰውና ዕቃ ስለሚጭኑ በትራፊክ አደጋ ሕይወቴን ወይም አካሌን ባጣስ? በሚል ስጋት።

ረዳቶቹ የእግር መቆሚያ እስከማይኖር ድረስ ካልጫኑ የጫኑ ስለማይመስላቸው ሕጉን ተከትለው በትክክል የሚሠሩ የትራፊክ ፖሊሶች ካሉ እነሱን እስኪያልፉ ወይም ከመናኸሪያ እስኪወጡ ድረስ በመቀመጫ ልክ ይጭናሉ። ከመናኸሪያ ከወጡና በትክክል የሚሠሩ ፖሊሶች አለመኖራቸውን ካረጋገጡ ተሳፋሪው የእግር መረገጫ እስኪያጣ ድረስ ይጭናሉ።

መኪናው ከአቅሙ በላይ ከጫነ ለትራፊክ አደጋ ሊያጋልጥ ይችላል ብለው የሰጉ አንዳንድ ተሳፋሪዎች ሲጠይቁም ከረዳቶቹና ከአሽከርካሪዎቹ የሚሰጣቸው መልስ "ምን አገባህ" ("ምን አገባሽ") ስለሚባሉ ደፍሮ የሚጠይቅ አይኖርም። ተሳፋሪዎቹ ደፍረው ከጠየቁም "ካልተመቸህ ውረድ" ("ካልተመቸሽ ውረጅ") ስለሚባሉ ፈጣሪን በመማፀን ከመጓዝ በስተቀር ሌላ ምርጫ አይኖራቸውም። ለዚያውም ደግ ረዳትና ሹፌር ከገጠማቸው እንጂ ከምን አገባህ በላይ ስድብና ግልምጫም ሊከተል ይችላል።

ለመሆኑ የትራንስፖርትና የታክሲ የአገልግሎት ታሪፍ እና የተሽከርካሪውን የመጫን አቅም የሚቆጣጠረው ማን ነው? የሚለው ጥያቄ የሚያጭርብኝ ለዚህ ነው። እናንተስ ራሳችሁን ጠይቃችሁ ታውቁ ይሆን? 12 እና 14 ሰዎችን እንዲጭን የተፈቀደለት ተሽከርካሪ 18 ሰው ጭኖ 20 ካልሞላ ስለማይንቀሳቀስ በሽተኞች፣ ሕጻናት እና ነፍሰ ጡር እናቶች ሲጨነቁ ማየት የተለመደ ተግባር በመሆኑ ሌላውን ተሳፋሪም ያስጨንቃል። ወንበሩ ማስቀመጥ የሚችለው ሁለት ሰዎችን በመሆኑ ሦስተኛ ተሳፋሪ አላስቀምጥም የሚል ተሳፋሪ ካለም የሚደርስበት ግልምጫና ዘለፋ አይጣል ነው።

በታክሲው ውስጥ የተጫኑት ተሳፋሪዎች ደኅንነት ግድ ሳይሰጠው መንገድ ላይ የቆሙ ሰዎች ስላዩ ብቻ መኪናው ቆሞ እንዲጭን ምልክት የሚሠጠውን ረዳት እና መኪናውን አቁሞ የሚጭነውን አሽከርካሪ በዓይነ ሕሊናችሁ ስታስታውሱ ጨንቋችሁ አያውቅም? አንዳንድ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች ሰዎችን አጭቀው በመጫን ስለሚሰበስቡት ገንዘብ እንጂ ለተሳፋሪዎቹ ደኅንነት ግድ ስለማይሰጣቸው ተሳፋሪ ባዩ ቁጥር አስቁመው ይጭናሉ።

ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ሥራውን ለማከናወን የሚተጋ የትራፊክ ፖሊስ አሽከርካሪውን ለምን ትርፍ ጫንክ ብሎ መጠየቅ ሲጀምር አማላጁ ብዙ ነው። አለበለዚያም "ሰሞኑን ዓመት በዓል ደረሰ እንዴ! ምነው አንቀዠቀዠው?" ይሄ የትራፊክ ፖሊስ ምነው ችክ አለ? ብለው የሚሳለቁ እና የሚያሽሟጥጡ ተሳፋሪዎችም ጥቂት አይደሉም።

ከታሪፍ በላይ ከፍለው የተሳፈሩ ተሳፋሪዎችን የትራፊክ ፖሊሱ ወይም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪው ሲጠይቃቸው የሚናገሩት በትክክለኛው ታሪፍ እንደከፈሉ ነው እንጂ ከታሪፍ በላይ እንደከፈሉ አይናገሩም። አንዴ ምን ሆነ መሰላችሁ፤ ሁላችንም ተሳፋሪዎች ከታሪፍ በላይ ከፍለን እየተጓዝን ሳለ ተቆጣጣሪዎች ድንገት አስቁመው የከፈልነውን ታሪፍ ሲጠይቁን ፤ ከፊት ከተቀመጡት ሰዎች አብዛኛዎቹ በታሪፉ መሠረት እንደከፈሉ ሲናገሩ አንዲት ተሳፋሪ የከፈለችውን በትክክል ተናገረች። ከአሽከርካሪው፤ ከረዳቱና ከሌሎች ተሳፋሪዎች የወረደባት ትችትና ግልምጫ ትዝ ይለኛል።

አንዳንድ ቸልተኛ የትራፊክ ፖሊሶች ባሉባቸው አካባቢዎችም ቁጥጥሩ አነስተኛ በመሆኑ የተሽከርካሪውን የመጫን እቅምና ታሪፉን የሚጠይቁ የትራፊክ ፖሊሶች ጥቂት በመሆናቸው ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ በመቀመጥ የሚሄድበት አጋጣሚ ብዙ ነው። እንዲህ ሲባል ግን በየመንገዱ ቆመው የትራፊክ ፍሰቱ እንዳይስተጓጎል ሥራቸውን በአግባቡ የሚያከናውኑ ትራፊክ ፖሊሶች የሉም ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ይያዝልኝ።

ችግሩ የአሽርካሪዎችና ረዳቶች ብቻ ነው ብሎ መደምደምም ስህተት ይመስለኛል። ምክንያቱም አንዳንድ ተሳፋሪዎች ተሽከርካሪው አለመሙላቱን እያዩም ወደኋላ ሄደው ላለመቀመጥ ሁለት ሰው ከሚያስቀመጠው ወንበር ቀድመው ሦስተኛ ሆነው ሲቀመጡ ረዳቱ ወደ ኋላ ሄደው እንዲቀመጡ ሲጠየቃቸው ከረዳቱ ጋር ጭቅጭቅ የሚገጥሙ፤ ተሽከርካሪው ከአፍ እስከ ገደፉ መሙላቱን እያዩ ሌላ ተሳፋሪ ሦስተኛ ሆኖ እንዲቀመጥ የሚጋብዙ ካልተሳፈርን ብለው የሚታገሉ ተሳፋሪዎችም አሉ። የትራንስፖርት እጥረቱ አስገድዷቸው የሚሳፈሩትን ሳይጨምር ማለቴ ነው።

> **ነፍሰ ጡር እናቶችንና ትንሽ ወፈር ያሉ ሰዎችን ሲያዩም ለእርስዎ አይመችዎትም በማለት የሚያሳፍሩ ረዳቶችም አሉ። ለምን ከተባለ እነዚህ ሰዎች ከተሳፈሩ ሁለት ሰዎችን በሚያስቀምጠው ወንበር ሦስተኛ ተሳፋሪ ማስቀመጥ አንችልም ብለው ስለሚያስቡ ነው**

ሌሎች ተሳፋሪዎች ደግሞ ሁለት ተሳፋሪ በሚያስቀምጠው ወንበር ረዳቱ ሦስተኛ ተቀመጡ ስላላቸው ብቻ መብት ነው ብለው ስለሚያስቡ ቀድመው የተቀመጡ ሰዎችን "ጠጋ በል" ወይም "ጠጋ በይ" ብለው ካልተጠጉላቸው በግልምጫ የሚደባልቁ፤ የተሳፋሪው መብት ከማስጠበቅ ይልቅ፤ የሕገወጥ አሳፋሪዎችን ድርጊት የሚተባበሩ ተሳፋሪዎች አሉ።

በተለይ በሥራ መግቢያና መውጫ ተደራርቦ የመቀመጥ መጠኑ ይጨምራል። መንግሥት ለመንግሥት ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ባያዘጋጅ ኖሮ በሥራ መግቢያና መውጫ ምን ሊፈጠር ይችል እንደነበርም አስቡት። ይህም ሆኖ ግን በሥራ መግቢያና መውጫ፤ እንዲሁም በተማሪዎች መግቢያና መውጫ ሰዓት ረጅም ሰልፍ ማየት የተለመደ ነው።

በመግቢያና በመውጫ ሰዓት መንግሥት ለመንግሥት ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ማዘጋጀቱ ለመንግሥት ሠራተኛው ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ የሌላውንም የትራንስፖርት ችግር ፈትቷል ማለት ስለሚቻል በዚህ ዘመን ከተሠሩት መልካም ሥራዎች ውስጥ ይህ ተግባር መንግሥትን ከሚያስመሰግኑት ውስጥ ይመደባል።

ከመሸ በኋላ ለመንቀሳቀስ የፈለገ ተሳፋሪ በኪሱ ተጨማሪ ገንዘብ ስለመያዙ እርግጠኛ መሆን አለበት፤ በቂ ገንዘብ ካልያዘ ግን ትራንስፖርት አጥቶ ለችግር ሊጋለጥ ይችላል። ለ8 ብር መንገድ 2 ብር ስለማይመለስለት 10 ብር መክፈል የተለመደ ቢሆንም በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓትና መሸት ሲል የትም 20 ብር ነው በሚለው ብሂላቸው አንድ ፌርማታ ቢሄድም እንኳን 20 ብር ካልከፈልክ ተብሎ ተሳፋሪው ራሱ ባወጣው ተመን 10 ብር ልክፈል ቢል የሚሰማው የለም።

ከአዲስ አበባ ውጭ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጡ ውለው ማታ ማታ ወደ አዲስ አበባ መጥተው አገልግሎት የሚሠጡ ተሽከርካሪዎች ከወንበሩ ሁለትና ሦስት እጥፍ የሚበልጡ ሰዎች ቆመው እንዲሄዱ ሲፈርዱባቸው ማየትም የተለመደ ነው። እነዚህ ተሽከርካሪዎች ብዙ ተሳፋሪዎችን ስለሚጭኑ መቆሚያ እንጂ መያዣ ስለማይገኝ ተሳፋሪዎች እርስ በእርሳቸው ከወዲያ ወዲህ እየተጋፉ እና ከወንበር ጋር እየተጋጩ መሄድም የተለመደ ነው።

ቅርብ ለመውረድ በትናንሽ ኩሪሲዎች የተቀመጡ ተሳፋሪዎች አዲስ ተሳፋሪ በመጣ ቁጥር ደጋግመው ለመውረድና ለመውጣት ስለሚገደዱ መንታፊዎች በኪሳቸው የያዙትን ሞባይል እና ገንዘብ ሳይወስዱባቸው ወደ ቤታቸው ከገቡም ተመስገን ያሰኛል። በዚህ ሁኔታ የተጓዙ ተሳፋሪዎችን ከታሪፍ በላይ ማስከፈል ግን ሕሊና ቢስነት ነው።

ነፍሰ ጡር እናቶችንና ትንሽ ወፈር ያሉ ሰዎችን ሲያዩም ለእርስዎ አይመችዎትም በማለት የሚያሳፍሩ ረዳቶችም አሉ። ለምን ከተባለ እነዚህ ሰዎች ከተሳፈሩ ሁለት ሰዎችን በሚያስቀምጠው ወንበር ሦስተኛ ተሳፋሪ ማስቀመጥ አንችልም ብለው ስለሚያስቡ ነው።

መሸት ካለም "ቅርብ የትም 20 ብር ወይም 30 ብር ነው" የሚለው ማስታወቂያም የተለመደ ነው። ተሳፋሪዎች ለምን ብለው ከጠየቁ "ካልተመቸህ ውረድ" ("ካልተመሸ ውረጅ") ይባላሉ፤ አልወርድም ብሎ መብቱን ከጠየቀም የስድብ ውርጅብኝ ይወርድታል።

ተሳፋሪዎችም በሚነሳው ጭቅጭቅ ጊዜያቸውን ላለማባከን፤ ረዳቱ ያሰባትን ሳንቲም ላለማጣት፣ ሾፌሩ ለምን ተነካሁ በሚል የሚነሳውን ጭቅጭቅ ስለሚፈሩ ዝምታን ይመርጣሉ። ጭቅጭቅ ከተነሳም ጭቅጭቁ ተውትና በሠላም እንሂድበት የሚለው ተማፅኖም ለረዳቶችና አሽከርካሪዎች የልብ ልብ የሰጣቸው ይመስለኛል።

ልጆች ይዛ የምትጓዝ እናት ልጇን ከአጠገቧ ብታስቀምጥ እንኳን ረዳቱ ገና ሲያያት ለልጅሽም ትከፍያለሽ የሚል ማስጠንቀቂያ ስለሚሰጣት መውረድ ወይም መክፈል ነው ምርጫዋ። ተሳፋሪዎች መካከል አንዱ ወንበሩ እኮ ለሁለት ሰዎች እንጂ ለሦስት ሰዎች አልተሠራም ብሎ ከጠየቀም ቅድም ስትገባ ነግሬያታለሁ ያኔ መውረድ ትችል ነበር የሚሉ ረዳቶችም አሉ።

ከዚያ በኋላ እያንዳንዱ እጁን ከአፉ ላይ ጭኖ ከመጓዝ በስተቀር የሚጠይቅ ተሳፋሪ አይኖርም። በተለይ የዘወትር ተጓዥ ከሆኑ ሁሌም እንደሚያመናጭቋቸውና እንደሚያንጓጧቸው ስለሚያውቁ ከዚህ በላይ መከራከር አይፈልጉም።

በመላ ሀገሪቱ ያለውን የትራንስፖርት ችግር ለመቅረፍ በእያንዳንዱ ከተማ ያለ የትራንስፖርት ኃላፊ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ ቢኖርበትም ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ግን የብዙ ባለድርሻ አካላትን ርብርብ የሚጠይቅ ይመስለኛል።

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ያለውን የትራንስፖርት ችግር ለመፍታት የከተማ አስተዳደሩ የአንበሳና የሸገር አውቶቡሶችን አሰማርቶ፣ ምልልሳቸውን ማፍጠንና እንቅስቃሴያቸውን መከታተል መፍትሔ ይመስለኛል። የዛሬን አበቃሁ ፤ቸር እንሰንብት!

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ብርቱዋ እናት

እፀገነት አክሊሉ

በተሽከርካሪ ጭስ እና የድምፅ ብክለት የምትታወቀው አዲስ አበባን ወደኋላ ትተን ሽቅብ እየወጣን፤ ከመሬት ወለል በላይ 3 ሺ 200 ከፍታ ላይ እንገኛለን። ከሽሮ ሜዳ ተነስቶ እንጦጦ ማርያም በሚዘልቀው ሰፊ አስፋልት ሽቅብ ወጣን። በዚያ ተራራማ ስፍራ ቁልቁል ሲመለከቱ በሰፊ ብራና ላይ እንደተሳለ የከተማ አምሳያ አዲስ አበባ ቁልጭ ብላ ትታያለች።

አንዳንዱ የሚኖርባት ከተማ ይበልጥ በግልጽ እንድትታየው በኮረብታው ላይ ወጥቶ እጁን እየጠቆመ ያ ሕንጻ ያኛውስ አካባቢ የት ነው? እያለ ይጠይቃል። ገሚሱ መልስ ይሰጣል። ቅኝታችንን ቀጥለናል፤ መዳረሻችን ግን የብዙዎች ተስፋ ሊሆን ወደተገነባው ተቋም ነውና ጉዟችን አላበቃም። እንጦጦ ማርያም ስንደርስ ወደቀኝ ታጥፈን ገባን። ሌላ አዲስ የአስፋልት መንገድ ተቀበለን። የምንሄድበትን ቦታ በትክክል አናውቀውም ነበርና ሰዎችን እየጠየቅን ጉዟችንን ቀጠልን።

ፕሮጀክቶቹ በዋነኛነት በአካባቢው እንጨት ከጫካ በመልቀም ለሚተዳደሩ የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጀምረው የተጠናቀቁም የልማት ሥራዎች ነበሩ። ፕሮጀክቱ ባለ 5 ወለል አምስት ሕንፃዎች የያዘ ሲሆን፤ እነዚህ ሕንጻዎች ደግሞ 200 አባወራዎችን የሚይዙ፣ ሁሉም ቤቶች ዘመናዊ ሆነው የተሠሩ ከመሆናቸውም በላይ የመኖሪያ መንደሩ ውብ ምድረ ግቢ አረንጓዴ ስፍራዎች አካቶ በ 14 ሺ 625 ካሬ ሜትር ላይ እንዲያርፍ የሆነ ነው።

ይኸው ፕሮጀክት ጉለሌ እንጀራ ማዕከልን ይዟል፤ ይህ ለከተማዋ ሁለተኛው የእንጀራ ፋብሪካ ሲሆን፤ በአካባቢው እንጨት በመልቀም ለሚተዳደሩ 551 እናቶች የሥራ እድል የፈጠረ ነው። የእንጀራ ማዕከሉ በውስጡ ሁለት የእንጀራ መጋገሪያ ሕንጻዎች፣ የሕጻናት ማቆያ፣ የእህል ማከማቻ፣ ወፍጮ ቤት እንዲሁም ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን ያካተተ ነው።

450 ዘመናዊ የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ የተገጠመለት ይህ ማዕከል፤ ዘመናዊ የሊጥ ማቡኪያና ዘመናዊ የአብሲት መጣያ ማሽን፣ ሁለት ወፍጮዎች አሉት። 551 እናቶች በሁለት ፈረቃ ተከፍለው ይሠሩበታል ተብሎ ይጠበቃል።

በእንጀራ ማዕከሉ ውስጥ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው እናቶች ከዚህ በፊት በአካባቢው እንጨት በመልቀም ሲተዳደሩ የነበሩ፣ ምንም ገቢ የሌላቸው እና የኑሮ ጫና የበረታባቸው ናቸው።

ወይዘሮ ሠናይት ደምሴም በእድሜ ጠና ያሉ ሲሆን፤ የእዚህ እንጀራ መጋጋሪያ ፋብሪካ አባል ናቸው። ተወልደው ያደጉት ጋሞጎፋ ነው። በእናትና አባታቸው ቤት ከእህት ከወንድሞቻቸው ጋር እንደ ማንኛውም የአካባቢው ሕጻን ቢያድጉም የመማር እድልን ግን አላገኙም ነበር።

ወይዘሮ ሠናይት ተወልደው ባደጉባቸው የልጅነት ጊዜዎች ብዙ የማይረሱ ትዝታዎች አሏቸው። ከእኩዮቻቸው ጋር መጫወቱ መቦረቅ እንደ ሴት ልጅ ደግሞ ቤት ገብቶ እናትን ማገዙ በዓላት ሲመጡ የተለያዩ ምግቦችን እየተመገቡ በሀገር ሽማግሌዎች መልካም ምኞትን እየተለዋወጡ አክስት አጎት ጎረቤት ጋር እየተዘዋወሩ መብላት መጠጣት ብቻ ብዙ የማይረሷቸው ትዝታዎች ያሏቸው እናት ናቸው።

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ጋሞ ጎፋ ሆነው ከአዲስ አበባ ሰው ከመጣ እንደ ብርቅ ስለሚታይ አዲስ አበባ ምን ትመስላለች? ምን አለ? ከጎሞ ጎፋ በምን ትለያለች? የሚለውን ለመስማት የሚደረግ ግብግብን ሲያስቡት ያስቃቸዋል። ይሔ ሃሳብ ወደኋላ ጎተታቸው። ‹‹የትውልድ አካባቢዬ ጋሞ ጎፋ ለእኔ ትልቅ ትዝታዬ ነው በማለትም የኋሊት እያሰቡ መተከዝ ጀመሩ።››

በዚህ መልኩ በቤተሰብ በዘመድ አዝማድ በአብሮ አደግ ጓደኛ ተከበው ይኑሩ እንጂ አዲስ አበባ ይሉት ሀገርን ማየት ግን ሕልማቸው ነበር። በእርግጥ ሕልሙ የእሳቸው ብቻ ሳይሆን የሁሉ የእድሜ እኩዮቻቸው የመጨረሻ ግብ አዲስ አበባ ገብቶ ዘናጭ አማርኛ ተናጋሪ ሠርቶ ብዙ ብር የሚያገኝ መሆን ነበር።

".....እውነት ለመናገር በሀገሬ ላይ ስኖር ያን ያህል ጎሎብኛል የምለው ነገር አልነበረም። ያደግነው እንደ ሁሉም የአካባቢው ታዳጊዎች ገጠር ያፈራውን ሁሉ በልተን ጠጥተን ከብት ጠብቀን ቤተሰብ በሥራ ረድተን ነው። ነገር ግን ደግሞ አዲስ አበባን ማየት ብሎም ሠርቶ ሀብታም መሆን እንፈልግ ነበር።" በማለት ሁኔታውን በማስታወስ ይናገራሉ።

በሞቀ የጉጉታቸው ዘመን ገና በሕፃንነታቸው ሄደው ያላዩዋትን አዲስ አበባ እድሜያቸው ከፍ ሲልና ችግሮችን እቋቋማለሁ ብለው በሚያስቡበት እድሜ ላይ ሲደርሱ አዲስ አበባ መግባታቸው አልቀረም። ብር እንደ አፈር ይታፈስባታል፤ ዘመናዊ ኑሮ ይኖርባታል፤ የተባለችውን አዲስ አበባም ለማየት አክስታቸው ዘንድ ዘለቁ።

".......አዲስ አበባ የመጣሁት በልጅነቴ፤ አንድ ብር ከ 90 ሳንቲም ትራንስፖርት ከፍዬ ነው። ስመጣም በጣም ደስ እያለኝ ሠርቼ ሀብታም እሆናለሁ ብዬ እየጓጓሁ ነበር። ከምንም በላይ ደግሞ አማርኛ ቋንቋን አቀላጥፎ መናገር ይቻላል ስላሉኝ፤ የመጣሁት እሱንም ለመልመድ በጉጉትና በከፍተኛ ፍላጎት ነው። ከመጣሁ በኋላም ያረፍኩት በቀጥታ አክስቴ ቤት ነበር "ይላሉ ወይዘሮ ሠናይት።

ወይዘሮ ሠናይት አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ፤ ያረፉባቸው አክስታቸው የበቆሎ ዱቄት እያዘጋጁ አስፈጭተው ለገበያ የሚያቀርቡ ነበሩና እርሳቸውም የተቀላቀሉት የሥራ ዘርፍ ይኸው የዱቄት ሥራ ነበር። ነገር ግን አክስታቸው እርሳቸውን ጨምሮ የራሳቸውንም ልጆች በዚህ ሥራና በሚያገኙት ገቢ ማስተዳደር እጅጉን ከብዷቸው ነበር። እናም ሌላ የሥራ ዘርፍ መቀየር እንዳለባቸው በማሰብ ፊታቸውን ወደ እንጦጦ ጫካ አዞሩ።

እንጦጦ ጫካ እንደ ወይዘሮ ሠናይት አክስት ያሉ በርካታ እናቶች ሌሊት ተነስተው ከጅብ ጋር ተጋፍተው የሚሠሩበት ቦታ ነው። ጅብ ብቻ አይደለም፤ በጫካ ውስጥ የሚደርስባቸውን ፆታዊ ጥቃት ሁሉ ተቋቁመው ብርድ እና ፀሐይ ሳይበግራቸው፤ እንጨት ለቅመው ያንን ቁልቁለት ካዘሉት እንጨት ጋር የሚወድቁ እየመሰሉ ወርደው ዳገቱንም ወጥተው ልጆቻቸውን የሚያሳድጉበት ነው። ለእነወይዘሮ ሠናይት ቦታው ቤታቸውን የሚደግፉበት የብዙዎች ባለውለታ ሊባል የሚችል ነው።

እናም የወይዘሮ ሠናይት አክስት የዱቄት ሽያጩ አልሆን አላዋጣ ሲላቸው በቀጥታ እንግዳዋን የእህታቸውን ልጅ ሠናይትን ይዘው ያመሩት ወደዚሁ ጫካ ነው። በጫካውም እንጨት እየለቀሙ መሸጥን መተዳደሪያቸው አደረጉት።

"........እንግዲህ ብር ይታፈስባታል የተባለችው አዲስ አበባ እንደ ጠበኳት ባላገኛትም ባለው ሁኔታ ራሴን ማስተዳደር ነበረብኝና አክስቴን ተከትዬ እንጦጦ ጫካ ገባሁ። በዛም ሌሊት ወጥተን እንጨት እየለቀምን አስረን ተሸክመን ወደከተማ እያመጣን ሁለትና ሦስት ብር እየሸጥን መኖር ጀመርን" ይላሉ።

በእዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ግን ወይዘሮ ሠናይት ትዳር መመሥረትን አሰቡ፤ በሻማ ሥራ የሚተዳደሩት የትዳር ጓደኛቸውንም አገኙ። አሁን የባሰ ኑሮ እየከበደ የቤተሰብ ኃላፊነት እየሰፋ ወይዘሮ ሠናይትም ከቀደመው ጊዜ በይበልጥ እየተቸገሩና እየተማረሩ ቢመጡም፤ ኑሮን ማሸነፍ ግድ ነበርና ሳይታክቱ እንጨት ለቀማቸውን ገፉበት።

".......ባለቤቴን የተዋወቅሁት አክስቴ ጋር ዱቄት እየፈጨሁ በምሸጥበት ጊዜ ነው። በወቅቱ ልጅም ስለነበርኩ መልኬም ያምር ነበር። ወድጃታለሁ አስተዳድራታለሁ ብሎ ከአክስቴ ቤት ወጥቼ ወደ ትዳር ገባሁኝ። ከተጋባን በኋላ ግን እንደቃሉ መሆን አልቻለም። በሚፈለገው ልክም ቤቱን የሚያስተዳደር ሰው አልነበረም። እኔም ቁጭ ብዬ አልራብም በማለት ከአክስቴ ጋር ጀምሬው የነበረውን የጫካ እንጨት ለቀማ ሥራ ቀጠልኩበት። በወቅቱ እሱ ሻማ እየሠራ ይሸጥ ነበር። ብቻ ትዳር ጥሩ ነው። በሚል እየተቸገርንም ቢሆን አብረን መኖር ቀጠልን።" ይላሉ።



ወይዘሮ ሠናይት ደምሴ

> "........ከንቲባችን በእንጦጦ ጫካ ውስጥ የእለት ጉርሳችንን ለማግኘት እንባዝን የነበርንን ሴቶች ራስ ለማስቻል በሚል ይህንን የመሰለ ፕሮጀክት ነድፈው ወደሥራ አስገብተውልናል። ዛሬ ላይ ከሥራው ባሻገር የምንውልበት ቦታ በራሱ ጤና የሚሰጥ ነው። እኔና መሰሎቼ እንጀራ እንጋግራለን እንሸጣለን በዛም የምናገኘውን ገቢም ተካፍለን ኑሯችንን እንደጉማለን ብለን እየሠራን ነው" የወይዘሮ ሠናይት ተስፋ ነው።

ከትዳር በኋላ አብዛኛው ባለትዳር እንደሚያደርገው ልጅ መጣ ወይዘሮ ሠናይትም ነፍሰጡር ሆኑ። በዚህን ጊዜ ባለቤታቸው በይበልጥ ተቀየሩ ወይዘሮ ሠናይትም ያረገዙትን ልጅ ወለዱ። ይህንን ጊዜ ባለቤታቸው ውጪ ውጪ ማየት ጀመሩ። እጅ ያልሰጡት ወይዘሮ ሠናይት የወለዷት ልጃቸው ጠንከር እስከምትል ድረስ ጫካ መሄዳቸውን ተውና በቤታቸው ውስጥ ዳቦ (ሸልጦ) እየጋገሩ መሸጥ ጀመሩ።

"........ያረገዝኩት እንደ አገባሁ ነው። አሁን የመጀመሪያ ልጄ እኩያዬ ትመስላለች። ያገባሁት ሰው ያን ያህል ቤቱን የሚወድና የሚያስተዳድር ባይሆንም፤ በሚመጣበት ጊዜ ብቻ የባልነት ተግባሩን ፈጽሞ ይሔዳል። በዚህ ሁኔታ እኔም በላይ በላይ ስምንት ልጆችን ወለድኩ። እርሱም ከተለያዩ ሴቶች ጋር ሲሄድና ልጅ ሲወልድ እንደዚህ የምታደርገው ለምንድ ነው? ስለው ይደበድበኝ ነበር። አንገቴን ደፍቼ ስምንት ያህል ልጆቼን ማሳደጌን ቀጠልኩ " ይላሉ።

ወይዘሮ ሠናይት አራስ ሲሆኑ፤ በቤታቸው ዳቦ ጋግረው እየሸጡ ጠንከር ሲሉ ጫካ ሄደው ቅጠል ለቅመው እየሸጡ ብቻቸውን በሚባል ደረጃ ልጆቻቸውን ማሳደግን ተያያዙት። "......በወቅቱ ትምህርት በፈረቃ ስለነበር በተለይም ልጆች አደግ ካሉ በኋላ የከሰዓት ተማሪ የሆኑትን ጠዋት ጫካ አብረውኝ እንዲሄዱ በማድረግ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ብርቱዋ...

ከ7ኛ ገጽ የዞረ

እንጨት ለቅመን እንመጣለን። የከሰዓት ፈረቃ ተማሪዎቹ ማታ ሲመለሱ ደግሞ በቤት ውስጥ የጋገርኩትን ዳቦ አውጥተን መንገድ ዳር አብረን እንሸጣለን። ጠዋት ያልተሸጠውን ቅጠልም ከዳቦው ጋር አብረን እያወጣን መንገድ ላይ እየከመርን እንሸጣለን" በማለት ያለፉበትን የሕይወት ውጣ ውረድ ይናገራሉ።

ወይዘሮ ሠናይት ልጆቼ አባት አላቸው እርሱም ኃላፊነቱን ይወጣ ብለው የሚቀመጡ እናት አይደሉም። ከዛ ይልቅ የባለቤታቸውን መማገጥ ችለው ቤት መጥተው የሚደበድቧቸውንም ታግሰው የልጆቻቸው እድገት የእርሳቸው ብቻ ኃላፊነት እንደሆነ አስበው ደፋ ቀና ብለው ማሳደጋቸውን ቀጠሉ።

"...ስምንቱንም ልጆቼን ያሳደግኩት ብቻዬን ነው፤ የሚገርመው እኔ ልጆቼን ሳሳድግ ይከብደኝ የነበረው ነገር ሌሊት እንጨት ለቀማ ሄጄ የለቀምኩትን ሸጬ እቤት እስክመለስ ድረስ ልጆቼን የሚጠብቅልኝ ሰው አለማግኘቴ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሲያግዘኝ ግን ጥሩ ጎረቤቶች ስለነበሩኝ ልጆቼን እነሱ ቤት አስተኝቼ እሄዳለሁ። ስመለስ ለእነሱም በቤታቸው ምግብ የሚያበስሉበት እንጨት ለቅሜ ይዤላቸው እሄዳለው፤ ውሃ የሚቀዳው ራቅ ካለ ቦኖ ስለነበር ለጎረቤቶቼ ረጅም ርቀት ሄጄ ውሃ ቀድቼ አመጣላቸው ነበር። እንዲህ እያልኩ ልጆቼ አደጉ።" ይላሉ።

ወይዘሮ ሠናይት ልጆቻቸውን እንዲህ በማሳደጋቸው ዛሬ ላይ ደስተኛ ቢሆኑም፤ በጫካ ያሳለፏቸው አስከፊ ጊዜያትን ሲያስታውሱ በእጅጉ ያዝናሉ፤ ይንገፈገፋሉም። ግን ምን ይደረግ ልብስ እና ጫማ ባይኖር ቀን ይሰጣል። ሆድ ግን አንድ ቀን ባዶውን ቢውል ማደሩ ይከብደዋል። ስለዚህ እኔም ሆንኩ ልጆቼ በረሃብ ማለቅ የለብንም ብዬ ሁሉንም ተቋቁሜ ለዓመታት በእንጦጦ ጫካ ውስጥ እንጨት ፍለጋ ከዛም ተሸክሜ ገዢ ፍለጋ ብዙ ተንከራትቻለሁ።» በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

".......ጫካ ውስጥ የሚፈራው አውሬ ብቻ አይደለም። አውሬ እንደውም ምንም አያደርገንም። ግን በጣም ብዙ ባለጌ ሰዎች አሉ። ሴትነታችንን የሚጠቀሙትን ደፋሪዎች ሁሉ ማለፍ ግድ ነው። ብዙ እናቶች ልጆች ሴቶች በተደጋጋሚ ፆታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። ብዙዎች ይደፈራሉ፤ ያለፍላጎታቸው ያረግዛሉ። አባቱን የማያውቁትን ቢያውቁትም ዳቦ የማይገዛላቸውን ሰው ልጆች ተቸግረው ያሳድጋሉ። ይህ እንግዲህ በእንጦጦ ጫካ ውስጥ ቅጠል በመልቀም የሚኖሩ ሴቶች ሕይወት ነው"በማለት ይንገፈገፋሉ።

‹‹በተለይም እንጨት ሲለቀም የደን ጠባቂ ተብለው በቦታው የሚቀመጡት ሰዎች ባልታሰበ ሰዓት ብቅ እያሉ ቀኑን ሙሉ ለፍተን ደክመን ያከማቸነውን እንጨት እርጥብ እንጨት ቀላቅለሻል በሚል ምክንያት ይወርሷቸዋል። በዚህ ጊዜ ለልጆች ዳቦ መግዣ እንኳን ይጠፋል። የተራቡ ልጆች ፊት ዳቦ ሳይዙ መገኘት እንዴት እንደሚከብድ ማንም ቢሆን የሚያውቀው ነው።›› ይላሉ።

‹‹...ነገር ግን የእለት ጉርሳችን በጫካው ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፤ ዛሬ ተወረሰብን ነገ አንሄድም አንልም። ከደጉ ያጋጥመን በእኛ ላይ ምንም አይድረስ በሠላም ገብተን እንውጣ ብለን ሲነጋ ወደዛው ጫካ እንሄዳለን። የዕድል ቀናችን ከሆነ ካሰብነውም በላይ ትርፍ አግኝተን እንገባለን። ዕድል ከእኛ ካልነበረች ደግሞ ዳግም ሊወረስብን ወይም ደግሞ ገዢ ልናጣ እንችላለን።›› በማለት ይናገራሉ።



‹‹ከሁሉም በላይ የክረምት ጊዜ የእኛን የጫካ እንጨት ለቀማ ያከፋዋል›› የሚሉት ወይዘሮ ሠናይት፤ ‹‹አካባቢው እንኳን በክረምት በበጋም ቀዝቃዛ እንዲሁም ጉም ነው። ክረምት ሲሆን ደግሞ ይብሳል። በዛ ላይ የምንለቅመው እንጨት እርጥብ ይሆናል። ልንሸከመው ስንል በጣም ይከብዳል። እንደምንም ብለን ወደ ከተማ ካወጣነው በኋላ በጅምላ የሚገዛን ሰው ላናገኝ እንችላለን። በዚህን ጊዜ ተሸክመን መንደር ለመንደር ዞረን ለመሸጥ እንገደዳለን። ይህ ደግሞ ለተለያዩ ሕመሞች አጋልጦናል።›› ይላሉ።

ወይዘሮ ሠናይት የኑሮ ክብደት፣ ልጆችን አርግዞ መውለድ ብቻ ሳይሆን ያልተመቻቸ ሕይወት ለበርካታ ጊዜያት በሕመም ውስጥ እንዲያሳልፉ እንዳደረጋቸው ያስታውሳሉ። ከአንጀት መታጠፍ ጀምሮ ብዙ ችግሮች ገጥመዋቸውም ተደጋጋሚ ቀዶ ሕክምና ማድረጋቸውንም ያብራራሉ። እነዚህ ክስተቶች ደግሞ ዛሬ ላይ ወይዘሮ ሠናይት ከእድሜ መግፋት ጋር ተደማምረው ወገባቸው በቀበቶ ግጥም ተደርጎ ታስሮ እንዲንቀሳቀሱ ምክንያት እንደሆናቸውም ያብራራሉ።

እንደወይዘሮ ሠናይት ገለፃ፤ ዛሬ ላይ መንግሥት ሴቶች በተለያየ መልክ ራሳቸውን እንዲችሉ ከወንዶች ጥገኝነት እንዲወጡ ብዙ ይሠራል። የተጠቀሙም ብዙዎች ናቸው። ከሁሉ በላይ ደግሞ ሕጻናት ተማሪዎች ለደንብ ልብስ ለደብተር ለሆድ ሳይጨነቁ ትምህርታቸውን እንዲማሩ አድርጓል። ያን ጊዜ በተለይም ልጆቻቸው ተማሪ ሆነው ይህ አልነበረም፤ መማር ከፈለጉ ቀን ሥራ መሥራት ድንጋይ መሸከም መላላክ ነበረባቸው። ምክንያቱም እርሳቸው ደብተር ገዝተው ዩኒፎርም አሟልተው ሆዳቸውንም ሞልተው ትምህርት ቤት መላክ አይችሉም ነበር።

‹‹የእኔ ልጆች ያለፉት በዚህ ሕይወት ውስጥ ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ በትምህርታቸው እንዳይገፉ ከዛ ይልቅ ሌሎች የሕይወት መንገዶችን በተለይም ከእኔ ጥገኝነት ወጥተው በልተው የሚያድሩባቸውን መንገዶች መፈለግን ጀመሩ።›› በማለት ይናጋራሉ።

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ያሳደጓቸው ልጆች፤ ምንም እንኳን ከኑሯቸው ተርፏቸው እናታቸውን ቁጭ አድርገው መጦር ደረጃ ላይ ባይደርሱም ሁሉም ለኑሯቸው የሚበቃ ሥራን እየሠሩ ቤተሰብ መሥርተው እየኖሩ እንዳሉ ያስረዳሉ።

"...እግዚአብሔር ይመስገን፤ ልጆቼን ለፍቼ ማሳደጌ ዛሬ ላይ በተመቻቸ ሁኔታም ባይሆን ያገኙትን እያካፈሉኝ ቢያንስ እንጨት ሳልሸከም እንድኖር አድርገውኛል። በዓለም ሲመጣ ያላቸውን ይሰጡኛል፤ አሁን ከእኔ ጋር ያለው የመጨረሻው ልጄ ብቻ ነው" ይላሉ።

ወይዘሮ ሠናይት ለዓመታት እንጨት የለቀሙበት እንጦጦ ጫካ ዛሬ ላይ ሊክሳቸው ያሰበ ይመስላል። የዘመናት ድካማቸውን አረፍ አድርጎ በስተርጅና የሚጦሩበትን ነገር እነሆም ብሷል። ዛሬ ወይዘሮ ሠናይትና መሰሎቻቸው ከዓመታት ድካም በኋላ እንደ ዜጋ የአቅማቸውን ሠርተው ጤናቸውና ሥራ ሰዓታቸው ተጠብቆ በሰርቪስ ደርሰው ተመልሰው የሚሠሩት ሥራ በአቅራቢያቸው ተተክሎላቸዋል። በቅርቡ የተመረቀው ጉለሌ የተቀናጀ የልማት ፕሮጀክት ለእነዚህ እናቶች በረከትን ይዞ የመጣ ይመስላል። በፕሮጀክቱ ውስጥ ከ551 በላይ የሚሆኑ እናቶችን እንጀራ በመጋገርና መሸጥ ሥራ ላይ አሰማርቶ ሊያግዛቸውም ዝግጅቱን አጠናቆ ተመርቆ ወደ ሥራ ከገባ ሳምንታትን አስቆጥሯል።

"....... እኔ የወለድኩት ቀላል አይደለም፤ እነሱን ለማሳደግ የለፋሁትንም የማውቀው እኔው ብቻ ነኝ። በተደጋጋሚ ቀዶ ሕክምና እድርጌያለሁ፤ ያ ግን ለመውለድ አይደለም ባለብኝ የሥራ ጫና ምክንያት አንጀቴ በተደጋጋሚ እየታጠፈ ስለነበር ነው። አሁን ላይ ይህ ሁሉ ነገር አቅሜን አሟጦታል። እናም ጫካ ወጥቼ እንጨት መልቀም የማልችልበት ደረጃ ላይ ደርሼ ነበር። ልጆቼ ያገኟትን ከቤተሰባቸውና ከልጆቻቸው እየቀነሱ ቢያካፍሉኝም፣ አነስተኛ የቀበሌ ቤት ቢኖረኝም ውሃ መብራት እድር የሚባሉትን ነገሮች ግን የምሸፍንበት እቸገራለሁ፤ እነዚህን ወጪዎቼን ለመሸፈን ያግዘኛል ያልኩትን ጥጥ እየፈተልኩ እየሸጥኩ ቀዳዳውን ለመሙላት እሞክር ነበር " ይላሉ ።

"........ከንቲባችን በእንጦጦ ጫካ ውስጥ የእለት ጉርሳችንን ለማግኘት እንባዝን የነበርንን ሴቶች ራስ ለማስቻል በሚል ይህንን የመሰለ ፕሮጀክት ነድፈው ወደሥራ አስገብተውልናል። ዛሬ ላይ ከሥራው ባሻገር የምንውልበት ቦታ በራሱ ጤና የሚሰጥ ነው። እኔና መሰሎቼ እንጀራ እንጋግራለን እንሸጣለን በዛም የምናገኘውን ገቢም ተካፍለን ኑሯችንን እንደጉማለን ብለን እየሠራን ነው" የወይዘሮ ሠናይት ተስፋ ነው።

ወይዘሮ ሠናይትና አብረዋቸው የሚሠሩት ከአራት መቶ ያላነሱ እንጨት ተሸካሚ ሴቶች የብርሃን ምልክትን አይተዋል። አሁን እንጨት ለቀማ ጫካ መሄድ እዛም ከሰውና ከአውሬ ጋር የሚያደርጉትን የሞት ሽረት ግብግብ ትተዋል። ከቤታቸው ሰብስቦ በሚያመጣቸው ሰርቪስ ሥራቸው ላይ ይገኛሉ፤ ሊጥ ማቡካት፣አብሲት መጣል፤ ሊጥ ቀድቶ ለጋጋሪዎች ማቀበል እንዲሁም እንጀራ መጋገር በሚል የሥራ ዝርዝራቸው ወጥቷል፤ በዚህ መሠረትም የግማሽ ቀን የሥራ ጊዜያቸውን አሳልፈው ወደ ቤተሰባቸው ወደ ልጆቻቸው በሰርቪሳቸው ይመለሳሉ።

"........እኔ ዛሬ ላይ ቆሜ ስሄድ ጤነኛ እመስላለሁ። ግን የምንቀሳቀሰው ወገቤን በቀበቶ ደግፌ ነው። ይህም ቢሆን ዛሬ ላይ ያለሁበትን ነገር ሳስበው በጣም ደስተኛ ነኝ። አሁን በክብር ሥራ ውዬ እየገባሁ ነው። ወደፊት ሥራው አድጎና ተጠናክሮ ሲሄድ ደግሞ ሕይወቴ በብዙ መልኩ እንደሚለወጥ እርግጠኛ ነኝ።" ይላሉ።

አሁን ላይ ወይዘሮ ሠናይት በእድሜያቸው እንዲሁም በጤና ሁኔታቸው ምክንያት እንደ ሌሎቹ ተሯሩጠው ማቡካት መጋገር ባይችሉም ልምዳቸውን ተጠቅመው ግን ስለ ቡኮው አብሲቱ እንዲሁም ስለሚጋገረው እንጀራ ጥራት እየተዘዋወሩ ይቆጣጠሩ ዘንድ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። ይህንን የሥራ ኃላፊነታቸውንም በአግባቡ ሲወጡም ተመልክተናል።

"........አሁን ያየነው እና የጀመርነው ሥራ ገና ጅምር ነው። ገንዘብ ወደማግኘት አልገባንም ግን የምናየው ነገር በራሱ ሳይበሉ የሚያጠግብ ሆኖብናል። ወደሥራ ብዬ ስመጣ እንዴት እንደምደሰት የማውቀው እኔ ነኝ" ይላሉ።

ወይዘሮ ሠናይት አብረዋቸው ለሚሠሩት እንጨት ተሸካሚዎች "......ምናልባት ዛሬ ላይ የምናገኘው ነገር ላይኖር ቢኖርም በቂ ላይሆን ይችላል፤ በዚህም ቤታችን ኑሯችን ጎሎም ይሆናል። ነገር ግን ጫካ ከአውሬ ጋር ተጋፍተን ሴትነታችንን አደጋ ውስጥ ከተን እንኖር ከነበረው ኑሮ ጋር ፍጹም አይገናኝም። በመሆኑ ሁሉም ሠራተኞች ዛሬን ብቻ ሳይሆን ነገን አርቆ ማየት አለባቸው። ዛሬ ብንቸገር ነገ እንለወጣለን ብለን ማሰብ ይገባናል" ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል- የጥገና ሂደቱ ምን ላይ ደረሰ?

**ዳግም ከበደ**

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ ውስጥ ግዙፍ ስፍራ የያዘች ጥንታዊት የእምነት ተቋም እንደሆነች ይታወቃል። የኢትዮጵያ በርካታ ታሪካዊ፣ ባሕላዊ፣ ሥነልቦናዊ ውቅርም ከዚሁ ጋር በእጅጉ ቁርኝት አለው። ይህንን እውነታ አጉልተው ከሚያሳዩ አስረጂዎች ውስጥ ዘመናትን ያስቆጠሩ ቅርሶች፣ ሥነ ጽሑፎች፣ የሥነ ጥበብ ውጤቶች ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ሀብቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ኢትዮጵያን በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ቅርሶች በተለይ በዓለም መድረክ ላይ ስናስተዋውቅ ጥንታዊቷ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያበረከተቻቸውን፣ ዛሬም ድረስ ጠብቃ ያቆየቻቸውን ሀብቶች ደምረን ነው። የላሊበላ፣ አክሱም ጽዮን፣ የይምርሀነ ክርስቶስ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም በርከት ያሉ ጥንታዊ ገዳማት፣ የብራና መጽሐፍት፣ የጥንት ቁሳዊ ሀብቶች እና ሌሎችም የማይዳሰሱና የሚዳሰሱ ቅርሶችን ይዘን ነው።

በዓለማችን ላይ በርካታ ጎብኚዎች ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ይዘት ያላቸው ቅርሶችን ለመመልከት ወደ ተለያዩ ሀገሮች ይጓዛሉ። ከእነዚህ ተመራጭ ስፍራዎች መካከል ደግሞ ኢትዮጵያ ቀዳሚዋ ነች። በግዕዝ የተፃፉ ድርሳናትን፣ የአያት ቅድመ አያቶቻችንን የሥልጣኔ ጥበብ የያዙ ብራናዎችን፣ የኪነ ሕንፃ ጥበብ፣ ተፈጥሮ እና ሃይማኖታዊ ምስጢራትን ሀገራችን ኢትዮጵያ በብዛት ይዛለች። አያሌ ቅርሶችም በወራሪዎች ከሀገር ውስጥ ተዘርፈው በዓለማችን ታላላቅ ሙዚየሞች ሲገበኙ ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህን በገንዘብ የማይተመኑ ታላላቅ ቅርሶችን እነዚህ አካላት በኩራት ሲያስጎበኙ ይስተዋላሉ፡፡ ኢትዮጵያም እነዚህን የማንነቷ መገለጫ ቅርሶች ለማስመለስ በርካታ ጥረቶች እያደረገች መሆናን መረጃዎች ያመለክታሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለዓለማችን ካበረከተቻቸው ሀብቶች ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀሱት ኪነ ሕንፃ እና ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ይገኛሉ። አብዛኞቹ ክፍለ ዘመናትን ወደኋላ የተሻገሩ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በርከት ያሉ አስርተ ዓመታትን ያስቆጠሩ ናቸው።

ከእነዚህ የእምነት ተቋማት (በኪነ ሕንፃ ቅርስ ከሚመደቡት) ውስጥ 92 ዓመታትን እድሜ ያስቆጠረው የመንበረ ፀባዎት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይገኝበታል። የዛሬ የባሕልና ቱሪዝም ዓምዳችንም በዚህ የእምነት ስፍራ የኪነ ሕንፃ ቅርስ ላይ ያተኩራል። ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ለማንሳት የወደድንበት ዋንኛው ምክንያትም በአራት ኪሎ እምብርት ላይ የሚገኘው ካቴድራሉ እያደረገ ያላው የቅርስ ጥገና መርሐ ግብር ነው።

ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን በኪነ ሕንፃ ውበቱ ማራኪ መሆኑ ተመስክሮለታል። የአምልኮ ሥነሥርዓት ከሚፈፅሙት ምዕመናን ውጪ በየእለቱም ከውጪም ሆነ ከሀገር ውስጥ በርካታ ጎብኚዎች ሊጎበኙት ወደ ስፍራው ይጎርፋሉ። በኢትዮጵያ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ታዋቂ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ እንዲያርፉ የሚደረጉትም በዚህ ታላቅ ስፍራ ነው። ለጎብኚዎች ልዩ ትርጉም ካላቸው የጉብኝት ቦታዎች አንዱም ይህ እንደሆነ ይነገራል። የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤትም ኪነ ሕንፃውን በቅርስነት መዝግቦት ልዩ ትኩረትና ጥበቃ እንዲደረግለት በትብብር እየሠራ ይገኛል።

ካቴድራሉ በአሁኑ ወቅት በቤተክርስቲያኗና በኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ጥገና እየተደረገለት ነው። የጥገና ሂደቱ ምን ላይ እንደደረሰ በቅርቡ በተሰጠ መግለጫ ላይ እንደተመለከተው፤ የካቴድራሉ ጥገና በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ሰብከት የመንበረ ፀባዎት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሚያዚያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም. በሰጠው በዚህ መግለጫ ላይ የካቴድራሉ አስተዳዳሪ ሊቀ ሥልጣናት



ቆሞስ አባ ሲራክ አድማሱ የኪነ ሕንፃ እድሳቱን አሁናዊ ሁኔታ በማስመልከት እንዳስታወቁት፤ አንድ ሀገር ሃይማኖት፣ ታሪክና ቅርስ ከሌለው ማንነቱ በሌሎች ዘንድ ሊታወቅ አይችልም። ቅርሶች ያለፈውን፣ ነባሩንና ተተኪውን ትውልድ የሚያገናኙ የትውልድ ድልድዮች ናቸው። ኢትዮጵያም ንዋይ ሊተምነው የማይችል የታሪክና የቅርስ ግምጃ ቤት ናት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በውስጧ በርካታ ሃይማኖታዊና ሀገራዊ ቅርሶች በመያዝ በሀገር በቀል እውቀቶቿ ለሀገሪቱ የሥልጣኔ ዐሻራ መሆን ችላለች። ለእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ቅርስና ልዕልና መነሻ በመሆን ትልቁን አስተዋፅዖ እያበረከቱ ከሚገኙት መካከልም ከቤተክርስቲያኗ የፈለቁት ሀብቶች መሆናቸው ዛሬም ሕያው ምስክሮች ናቸው።

‹‹የቀደሙት አባቶች ያቆዩትንና ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ እንድትታወቅ ያደረጉትን ቅርሶች ትናንት በነበሩበት ሁኔታ እንዲቆዩ ሊጠበቁና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል›› ያሉት አስተዳዳሪው፤ ከእነዚህ ቅርሶች መካከል አንዱ የሆነው የመንበረ ፀባዎት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መሆኑን ጠቅሰዋል።

ለካቴድራሉ ግንባታ መሠረት የተጣለው በወቅቱ ንጉሥ በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አማካኝነት በ1924 ዓ.ም. መሆኑን አስታውሰው፣ ይሁን እንጂ በፋሺስት ወረራ ጊዜ ለአምስት ዓመታት ግንባታው ተቋርጦ ቆይቷል ብለዋል። ከድል በኋላም ንጉሡ ዳግም ሥራው ተጀምሮ በከንቲባ ከበደ ተሰማ ተቆጣጣሪነት ግንባታው በ1936 ተጠናቅቆ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ተጀምሯል ያሉት አስተዳዳሪው፣ የግንባታው ሙሉ ወጪ የተሸፈነውም በንጉሡ አማካኝነት መሆኑን አመልክተዋል።

እንደ አስተዳዳሪው ገለፃ፤ ካቴድራሉ በእድሜ እርዝማኔ ምክንያት እድሳት ሳይደረግለት በመቆየቱ ውስጣዊና ውጫዊ የሕንፃው አካል ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት ቅርሱን ለችግር የሚያጋልጠው ሆኖ ተገኝቷል። ሁለንተናዊ ውበቱን፣ ቅርሱንና ይዘቱን እንደጠበቀ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ከቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በሀገሪቱ ባሉ ታዋቂ የቅርስ ጥናት ባለሙያዎች አማካኝነት ጥልቅ ጥናት ለአንድ ዓመት ከ4 ወር ተደርጎለታል። ግኝቱን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት የእድሳቱ ሥራ ተጀምሮ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ነው።

‹‹ካቴድራሉ በርካታ ቅርፃ ቅርፆች ያሉትና ውድ ከሆኑ የተለያዩ ቁሳቁስ የተገነባ ነው›› ያሉት አስተዳዳሪው፤ እድሳቱን ለማከናወን በቅርስ እድሳት የካበተ ልምድ ካለው ቫርኔሮ ከተባለ ድርጅት ጋር 172/የአንድ መቶ ሰባ ሁለት/ ሚሊዮን ብር የሥራ ውል ስምምነት መፈፀሙን ይናገራሉ። ክንውኑም በተፋጠነ መልኩ እየሄደ እንደሆነ ጠቅሰው፣ እድሳቱ በገንዘብ እጥረት ምክንያት እንዳይስተጓጎል በታሪኩና በቅርሱ ለማይደራደረው በሀገር ውስጥና በውጪ ለሚገኘው

**አንድ ሀገር ሃይማኖት፣ ታሪክና ቅርስ ከሌለው ማንነቱ በሌሎች ዘንድ ሊታወቅ አይችልም። ቅርሶች ያለፈውን፣ ነባሩንና ተተኪውን ትውልድ የሚያገናኙ የትውልድ ድልድዮች ናቸው። ኢትዮጵያም ንዋይ ሊተምነው የማይችል የታሪክና የቅርስ ግምጃ ቤት ናት**

ኢትዮጵያዊ ማሳወቅ ማስፈለጉን ያብራራሉ።

አብዛኛው ማኅበረሰባችን ካቴድራሉ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም እንዳለው፣ ምንም አይነት እርዳታ እንደማያስፈልገው አርጎ ያለምንም ተጨባጭ ማስረጃ የተዘገበበት ሁኔታ እና ከዚህ በመነሳትም ድጋፍ ለማድረግ ፍቃደኛ አለመሆኑ እየታየ ያለበት ሁኔታ የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደቱን ከምናስበው በላይ እጅግ ውስብስብ እና ፈታኝ አድርጎብናል ሲሉ አስተዳዳሪው ጠቁመዋል፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫው ያስፈለገበት አንደኛው ምክንያት ይሄው እንደሆነም ይናገራሉ።

ከተሳሳቱ ግንዛቤዎች መካከል ካቴድራሉ ዙሪያ ያሉትን ሕንጻዎች የካቴድራሉ ንብረት አድርጎ የመቁጠር ፣ ብዙ ባለሀብቶች የሚረዱት አድርጎ ማሰብ አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል። ስለሆነም በሀገር ውስጥም፣ ከሀገር ውጪም ያሉ ኢትዮጵያውያን ካቴድራሉ በዙሪያው ምንም አይነት የሚያከራየውና ገቢ የሚያገኝበት ሕንጻ እንደሌለው ፣ ዙሪያውን ያሉ ነዋሪዎች በልማት ምክንያት በመነሳታቸው ከሌሎች ከተማ ዳር አካባቢ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት ያነሰ ገቢ እንዳለው እንዲረዱላቸው አስገንዝበዋል፡፡

አስተዳዳሪው ጥገናው ከሦስት ወር በኋላ ሙሉ ለሙሉ እንደሚጠናቀቅ ጠቅሰው፣ ሥራው ሲጠናቀቅ በውሉ መሠረት የሚከፈል ጠፍቶ ያልተገባ እና ያልተፈለገ ችግር ውስጥ ላለመግባት ሕዝቡ የከተማዋ ታላቅ ቅርስ ለሆነው ካቴድራል እድሳት ማጠናቀቂያ የሚውል የገቢ ማሰባሰብ ላይ እንዲሳተፍ ጥሪ አስተላልፈዋል። እድሳቱን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ 85 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግም ገልፀዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በጥገናው እስካሁን ከተሠሩት ሥራዎች የመጀመሪያው የእድሳትና ጥገና ሥራ ነው፡፡ ከካቴድራሉ ሕንፃ መስቀል አንስቶ እስከ መሠረት ማጠናከር ድረስ በሚገኙ ሥራዎች መካከል ከተከናወኑ ሥራዎች ውስጥ የመዋቅር እድሳት በምድር ቤት ውስጥ የሚገኙ ምሰሶዎች ማጠናከር፣ የሚዛን ወለል ሙሉ ለሙሉ አፍርሶ የመሥራት ተግባር፣ የሕንፃው መካከለኛ ክፍል ላይ ከፍ ብሎ የሚገኘውን ስፍራና የውጪ ግድግዳ እድሳት፣ የልስን ሥራ፣ የውስጣዊ ክፍል ስዕል እድሳትና ሌሎችም ተሠርተዋል።

በኪነ ሕንፃ እድሳት ዘርፍ ደግሞ የሁለት የደውል ቤቶችና መስቀሎች እድሳት መሠራቱን የተናገሩት አስተዳዳሪው፣ የትልቁ መስቀል (ዶም) እንዲሁም የመካከለኛውና ትልቁ (ዶም) ጣሪያ የመዳብ ጥገና፣ የድንጋይ ጌጦች የመጀመሪያ አጠባ፣ የወንጌላውያንና የመላዕክት የሐውልት ቅርፃ ቅርፆች ፅዳት፣ የስዕል ጥገና ሥራ፣ የፍሳሽ መስመር ጥገና፣ የኤሌክትሪክ መስመር ጥገና፣ የዓውደ ምሕረት የባዞላ ንጣፍ መቀየር ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን አብራርተዋል።

አስተዳዳሪው ባለፉት 18 ወራት ወስጥ ከላይ የተዘረዘሩት ሥራዎች መከናወናቸውን ገልፀው፤ እነዚህም ከመሠረታዊው የቅርስ እድሳት ሥራዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ይናገራሉ። ቀጣይ ሥራውም በየጊዜው በባለሙያዎች ክትትል እየተደረገለት እስከ ፍፃሜው ድረስ እንደሚገልፅ አስታውቀዋል። በሂደቱም የሕንፃ ጥገና ሥራው 75 በመቶ መድረሱን ገልጸዋል።

በእድሳቱ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮች መኖራቸውን የሚያነሱት አስተዳዳሪው፤ የመጀመሪያው በውሉ መሠረት ሥራው ተጠናቅቆ የሚያልቅበት የጊዜ ገደብ መጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም እንደነበረም ተናግረዋል። የዶም ኮፐር ቀለም እና የውጪያዊ ግድግዳ ቀለም፣ ሞዛይኮች፣ መብራቶችና ጄነሬተር ከውጪ ሀገር የሚመጡ መሆናቸውን አመልክተው፣ እነዚህን ለማስገባት የውጪ ምንዛሪ እጥረት ማጋጠሙን ይናገራሉ። ምንዛሪውን ለማግኘት ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ቢቀርብም ለማግኘት መቸገራቸውን ይገልፃሉ። በዚህ ምክንያትም ጥገናው የሚጠናቀቅበት ጊዜ እንዲራዘምና ሦስት ወራት የጊዜ ገደብ እንዲጨመር መደረጉን ያስረዳሉ።

የካቴድራሉን እድሳት በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያ የሰጡት አስተዳዳሪው ለሥራው የሚውል መዋዕለ ንዋይ የማሰባሰብ መርሐ ግብርን የተመለከተ ጉዳይም አንስተዋል። ለዚህ ተብሎ የተቋቋመው ኮሚቴ ገንዘብ ለማሰባሰብ የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀመ እንደሆነ ገልፀዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የመጀመሪያው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራና የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቁስቀሳ ሥራ ነው። ሌላው ከአዲስ አበባ ባሕል ቱሪዝምና ኪነጥበብ ቢሮ ጋር በመተባበር በስካይ ላይት ሆቴል የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በማድረግ እስካሁን ድረስ 90 ሚሊዮን ብር ማሰባሰብ ተችሏል። በኢንተር ኮኒቲኔንታል ሆቴል መሰል የገንዘብ ማሰባሰቢያ ሥራ ተዘጋጅቷል። ይህ መርሐ ግብር በቀጥታ ስርጭት በመገናኛ ብዙኃን ገንዘብ የማሰባሰብ እቅድን ያካተተ ነው።


ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የአንድ ሙያ ሰዎች የአንድ ቀን እረፍት

**ዋለልኝ አየለ**


ብርሃኑ ዘሪሁን


ደበበ ሰይፉ

አንዳንድ የታሪክ አጋጣሚዎች መመሳሰል ያጋጥማቸዋል። ለምሳሌ በዚህ ሳምንት ሁለት አንጋፋ የሥነ ጽሑፍ ሰዎችን እናስታውሳለን። ልዩነቶች ቢኖሯቸውም ሁለቱም የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ናቸው። በሥነ ጽሑፉ ዓለም ውስጥ ስማቸው ተደጋግሞ የሚጠሩ ናቸው። ሁለቱም በትርጉም ውስጥ ጉልህ እና ልዩ ድርሻ አላቸው። እነዚህ ጉምቱ የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ብርሃኑ ዘሪሁን እና ደበበ ሰይፉ ናቸው። ሁለቱም ሕይወታቸው ያለፈው በዚህ ሳምንት ሚያዚያ 16 ቀን ሲሆን ዓመተ ምሕረቱ ግን የተለያየ ነው። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን እነዚህን ሁለት አንጋፋ የሥነ ጽሑፍ ሰዎች እናስታውሳለን።

### መምህር፣ ተርጓሚ፣ ጋዜጠኛ እና ደራሲ ብርሃኑ ዘሪሁን

ከልጅነቱ ጀምሮ ጎበዝ ተማሪ ነበር። በ1948 ዓ.ም ከተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ሲመረቅ አንደኛ በመውጣት የከፍተኛ ማዕረግ ተሸላሚ ሆኖ ነው። የከፍተኛ ውጤት ባለቤት በመሆኑ በዚያው በተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት መምህር ሆኖ ተቀጠረ። የተለያዩ የውጭ መጻሕፍትንም ያነብ ስለነበር አስተርጓሚ ሆኖም ሠርቷል። ለጋዜጠኝነት ሙያ ልዩ ፍቅር ስለነበረው በተለያዩ ጋዜጦች በጋዜጠኝነት ሠርቷል። የአንጋፋውና ዕለታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበር። መምህር፣ ተርጓሚ፣ ጋዜጠኛ እና ደራሲ ብርሃኑ ዘሪሁን!

ብርሃኑ ዘሪሁን በሥነ ጽሑፍ ሰዎች ዘንድ ካልሆነ በስተቀር በሙያዎቹ ልክ ያልተዘመረለት የብዙ ሙያ ባለቤት ነው። ይህን ሰው ያጣነው ከ37 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዚያ 16 ቀን 1979 ዓ.ም ነው። እነሆ በዋና አዘጋጅነት ሲመራው የነበረው ጋዜጣ ሕይወቱንና ሥራዎቹን ያስታውሳል።

ብርሃኑ የተወለደው በ1925 ዓ.ም ነው። አባቱ መሪጌታ ዘሪሁን መርሻ የቤተ ክህነት ሊቅ ስለነበሩ ለልጃቸው ትምህርት የሚጨነቁ ነበሩ። እናም ልጃቸው በቤት ውስጥ በእርሳቸው የሚሰጠውን ጨምሮ የቤተ ክህነት ትምህርት እንዲማር አድርገዋል።

የኢትዮጵያን ባሕላዊ፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን በቤተ ክህነት ትምህርት ከተከታተለ በኋላ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ገባ። ዘመናዊ ትምህርት ቤት ከገባ በኋላም ለንባብ ያለው ልዩ ፍቅርና የጽሑፍ ችሎታው መገለጥ ጀመረ። ብርሃኑ ከልጅነቱ ጀምሮ ልዩ የማንበብ ፍቅር እንደነበረው የሚያውቁት ሁሉ ይመሰክሩለታል። መጽሐፍትን የሚያነብ ብቻ ሳይሆን እንደ ምግብም የሚጠቀምባቸው ዓይነት ሰው ነበር ይባላል።

ጋዜጠኛና ጸሐፊ ጥበቡ በለጠ ስለብርሃኑ ዘሪሁን በሰንደቅ ጋዜጣ በፃፉት ጽሑፋቸው እንዳብራሩት፤ የብርሃኑን ቀልብ ከሳቡት ድርሳናት መካከል ዋነኞቹ ስለኢትዮጵያ ታሪክ የተፃፉት መጻሕፍት ናቸው። ከነዚህም መካከል አለቃ ዘነብ የፃፏቸው ታሪኮች ተጠቃሽ ናቸው። አለቃ ዘነብ በዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበሩ የዘመኑ ሊቅ ነበሩ። እርሳቸው የፃፉትና በዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ያተኮረው መጽሐፍ በብርሃኑ የሚወደድ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ብርሃኑ ‹‹መጽሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ›› የተሰኘችውን፣ ሃይማኖት ላይ መሠረት አድርጋ የተዘጋጀችውንና ከኢትዮጵያ የፍልስፍና ጽሑፎች መካከል አንዷ ተደርጋ የምትቆጠረውን የአለቃ ዘነብን መጽሐፍ በተደጋጋሚ አንብቧታል። የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ፣ የክብር ዶክተር ከበደ ሚካኤል እና የነጋድራስ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ መጻሕፍትም ለብርሃኑ የንባብ ፍቅርና እውቀት መሠረት እንደሆኑት ታሪኩ ያስረዳል።

ብርሃኑ በ1945 ዓ.ም ከተወለደባትና ብዙ እውቀትን ከገበየባት ጎንደር ከተማ ወደ አዲስ አበባ መጣ። በአዲስ አበባ ቆይታውም ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ገብቶ የሬዲዮ ቴክኒሻንነት ሙያ በመማር በ1948 ዓ.ም ላይ በዲፕሎማ ተመረቀ። የተመረቀውም በትምህርቱ ከፍተኛውን ውጤት አስመዝግቦና አንደኛ ደረጃን በመያዝ ተሸላሚ ሆኖ ነው።

ብርሃኑ የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበረበት ወቅት የታላላቅ የዓለማችንን ደራሲያን ሥራዎችን ለማንበብ ዕድሉን አገኘ፡ የዊሊያም ሼክስፒርን፣ የአሌክሳንደር ዱማስ ፔሬን፣ የቻርልስ ዲከንስን፣ የአሌክሳንደር ፑሽኪንን እና የሌሎችን ስመጥር ደራሲያን መጻሕፍትን አነበበ። በዚህም የንባብ ልምዱን እያጎለበተና እውቀቱንም እያሳደገ መጣ። በዚህ ጊዜ ነበር የማንበብ ብቻ ሳይሆን የመፃፍም ችሎታ ያለው ብርሃኑ በንባብ የተከማቸውን እውቀቱን በጽሑፍ ማውጣት የጀመረው። እዚያው ተግባረ-ዕድ ትምህርት ቤት ሲማር የትምህርት ቤቱ ልሳን የነበረችውና ‹‹ቴክኒ ኤኮ›› የተሰኘችው መጽሔት አዘጋጅ ሆኖ ሠርቷል።

ብርሃኑ ከተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ሲመረቅ ውጤቱ ከፍተኛ ስለነበር እዚያው በመምህርነት ተቀጠረ። ከማስተማር ሥራው ባሻገር ለተለያዩ ጋዜጦች መጻፍ ጀመረ። ከተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት በመልቀቅ በወቅቱ አጠራር የጦር ሚኒስቴር (የአሁኑ መከላከያ ሚኒስቴር) በሚባለው መሥሪያ ቤት በአስተርጓሚነት ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ። እዚያም ብዙ ሳይቆይ በ1952 ዓ.ም ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ተዘዋወረ።

በማስታወቂያ ሚኒስቴርም ‹‹የኢትዮጵያ ድምፅ›› ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነ። በወቅቱም ጋዜጣዋን ታዋቂ ከማድረጉም በላይ በብዙዎች ዘንድ የሚነበቡ መጣጥፎችንና ታሪኮችን በመፃፍ ዝነኛ እየሆነ መጣ። በመቀጠልም የ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነ። ከዚህ በኋላ የብርሃኑ ስምና ዝና እየገነነ መጣ፤ በበርካታ ኢትዮጵያውያን ልብም ውስጥ ገባ።

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ቦታ ሊሰጣቸው የሚገቡ ሥራዎችን ካበረከቱ ደራሲያን አንዱ የሆነው ደራሲ፣ ጸሐፌ ተውኔት እና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ዘሪሁን ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየበት 1979 ዓ.ም ድረስ 11 ልብ ወለድ ድርሰቶችንና ሦስት ተውኔቶችን ለተደራሲያኑ ያበረከተ ብዕረኛ ነው።

በ1952 ዓ.ም ‹‹የእንባ ደብዳቤዎች›› በተባለ ድርሰቱ ጉዞውን የጀመረው ብርሃኑ፤ ‹‹ድል ከሞት በኋላ››፣ ‹‹አማኑኤል ደርሶ መልስ››፣ ‹‹የበደል ፍጻሜ››፣ ‹‹ጨረቃ ስትወጣ›› እና ‹‹ብር አምባር ሰበረልዎ›› የተባሉትን ድርሰቶቹን አበርክቷል። በተጨማሪም ‹‹የቴዎድሮስ እንባ›› እና ‹‹የታንጉት ምስጢር›› የተባሉ ሁለት ታሪካዊ ልብ ወለዶችንና በወሎ ክፍለ ሀገር ተከስቶ የነበረውን ድርቅና የመንግሥትን ቢሮክራሲ ሕያው አድርጎ የከተበባቸውን ‹‹ማዕበል የአብዮት ዋዜማ››፣ ‹‹ማዕበል የአብዮት መባቻ›› እና ‹‹ማዕበል የአብዮት ማግስት›› የተባሉ ሦስት ልብወለዶችን አስነብቧል። እነዚህ የማዕበል ድርሰቶቹ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሦስት ተከታታይ የሆኑ መፃሐፍትን በማሳተም ረገድ ብርሃኑ ዘሪሁን በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ፈር ቀዳጅ ሆኖ እንዲጠቀስ አስችለውታል። ‹‹ጣጠኛው ተዋናይ›› እና ‹‹ባልቻ አባ ነፍሶ›› የተሰኙ ተውኔቶችንም ጽፎ ለመድረክ አብቅቷል።

በ1958 ዓ.ም ያሳተመው ‹‹የቴዎድሮስ እንባ›› የተሰኘው መጽሐፉ የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስን አነሳስና ለኢትዮጵያ የነበራቸውን ራዕይ ብሎም የሕይወታቸውን ፍፃሜ የሚያሳይ ነበር። ብርሃኑ ይህን መጽሐፍ ከመፃፉ አስቀድሞ በነበሩት ጊዜያት ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በይበልጥ የሚታወቁት በኃይለኛነታቸውና በጭካኔያቸው ስለነበር ውስጣዊ ስብዕናቸውና ሌሎች ባሕርዮቻቸው ጎልተው አይነገሩም ነበር። እናም ብርሃኑ ዘሪሁን ያልተነገሩትን የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ባሕርያት ወደ አደባባይ በማውጣት ንጉሠ ነገሥቱ ብሔራዊ ጀግና መሆናቸውን የሚገልፅ ድርሰት ጽፎ በማቅረቡ የበርካቶችን ቀልብ መሳብ ቻለ። ይህ ‹‹የቴዎድሮስ እንባ›› የተሰኘው ታሪክ በኋላ ወደ መድረክ ሥራ ተቀይሮ ከታላላቅ ትያትሮች ተርታ መሰለፍ ችሏል።

‹‹ድል ከሞት በኋላ›› የተሰኘው ሥራው የሌሎች ሕዝቦችን ታሪክ መተረኩ ከብርሃኑ ሥራዎችም ሆነ ከሌሎች በዘመኑና ከእሱም ቀድመው ከታተሙ ልብወለድ ድርሰቶች ልዩ እንደሆነ ይነገርለታል።

ሦስቱ ማዕበሎች እና ‹‹የታንጉት ምስጢር›› መጻሕፍቱ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ተተርከው ለሕዝብ በመቅረባቸው በበርካታ ኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ አሉ።

የኢትዮጵያን ደራሲዎች ታሪክ ‹‹Black Lions The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers›› በሚል ርዕስ የፃፉት ኖርዌያዊው ሩዶልፍ ሞልቬር፤ ብርሃኑ ዘሪሁንን ከኢትዮጵያ ታላላቅ ደራሲያን ተርታ አስቀምጠውታዋል።

ሀገርን እና ትውልድን በብዕሩ ቀለማት ሲዘክር የኖረው ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ዘሪሁን ሚያዚያ 16 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይቶ ሥርዓተ ቀብሩ በባለወልድ ቤተ ክርስቲያን ተፈፅሟል።

### ደበበ ሰይፉ

ገጣሚ፣ ፀሐፊ ተውኔት፣ ደራሲ፣ ሃያሲ፣ ተርጓሚ፣ መምህር እና የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪ ደበበ ሰይፉ ያረፈው በዚሁ ሳምንት ከ24 ዓመታት በፊት ሚያዚያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም ነው።

ደበበ ሰይፉ ሥራዎቹ በተደጋጋሚ የሚጠቀሱና በብዙ የሥነ ጽሑፍ ወዳጆች የተመሰከረለት ገጣሚ ነው። የግጥም ትሩፋቶቹ በአንድ ላይ ተሰባስበው ‹‹የብርሃን ፍቅር›› በሚል ርዕስ ታትመዋል። በ1992 ዓ.ም ደግሞ በሜጋ አሳታሚ ድርጅት አማካኝነት ‹‹ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ›› በሚል ርዕስ ሁለተኛዋ የሥነ ግጥም መፅሐፉ ታትማ ለንባብ በቅታለች።

ደበበ ሰይፉ ከገጣሚነቱ ባሻገር ሐያሲም ነበር። ያለፈውን ከአሁኑ ጋር እያነፃፀረ የሚያስረዳና የሚተነትን ባለሙያ ነው። የሂስ ጥበብን ከታደሉትና በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሂስ ጥበብ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ሰዎች መካከል ደበበ ሰይፉ አንዱ ነበር።

ደበበ የትያትር ጥበብ መምህር ከመሆኑም በላይ በዘርፉ ውስጥ ግዙፍ የሚባል አስተዋፅዖ አበርክቶ አልፏል። ደበበ በመድረክ ላይ የሚሠሩ ቴአትሮችንና የቴአትር ጽሑፎችን የያዟቸውን ሐሳቦች በመተንተንና ሒስ በመስጠት ለዘርፉ ዕድገት የበኩሉን ሚና ተጫውቷል።

ደበበ የቃላት ፈጣሪም ነው ይባልለታል። ለአብነት ያህል በትያትርና በሥነ ጽሑፍ ዘርፎች ውስጥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጠሪያ የሆኑ ሙያዊ ቃላትን ወደ አማርኛ በማምጣት አቻ የሆነ የአማርኛ ትርጉም በመስጠት ይታወቃል። በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ መጠሪያ የሆኑትንና ‹‹ገፀ ባህርይ››፣ ‹‹ሴራ››፣ ‹‹መቼት››፣ ‹‹ቃለ ተውኔት›› ... እየተባሉ የሚገለፁትን መጠሪያዎች የፈጠረው ደበበ ሰይፉ ነው።

ደበበ ለትያትር ትምህርት ዘርፍ ካበረከታቸው አስተዋፅዖዎች መካከል ለትምህርቱ መጐልበት ይረዳ ዘንድ በ1973 ዓ.ም ‹‹የቴአትር ጥበብ ከጸሐፌ ተውኔቱ አንፃር›› የሚል ርዕስ ያላት መጽሐፍ ማሳተሙ የሚጠቀስ ነው።

ደበበ ጸሐፌ ተውኔትም ነው። በርካታ ተውኔቶችን ጽፎ ለመድረክ አብቅቷል። አንዳንዶቹ ደግሞ ለበርካታ ጊዜያት ያህል በቴሌቪዥን ታይተውለታል። ደበበ ከጻፋቸውና ከተረጐማቸው ተውኔቶች መካከል ‹‹ከባሕር የወጣ ዓሣ››፣ ‹‹እናትና ልጆቹ››፣ ‹‹እነሱ እነሷ››፣ ‹‹ሳይቋጠር ሲተረተር››፣ ‹‹የሕፃን ሽማግሌ››፣ ‹‹ማክቤዝ››፣ ‹‹ክፍተት››፣ ‹‹እድምተኞቹ›› እና ‹‹ጋሊሊዮ ጋሊሊ›› ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪ በነበረባቸው ዓመታት በርካታ የምርምር ሥራዎችን አከናውኗል፤ ብዙ መጽሐፍትንም ጽፏል። በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ተቋም የጥናት መጽሔት አሳታሚ ኮሚቴ እና በኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊ በመሆን ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ መስፋፋት ሰፊ እገዛ አድርጓል። እነሆ በሥራዎቹም ታሪክ ሲዘከረው ይኖራል!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## የሙዚቃው አጥቢያ ኮከብ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

መሸቶ ሲነጋጋ፤ ጀንበር ጠልቆ ጀንበር ሲወጣ፤ የአጥቢያ ኮከብ ከአዲስ ሰማይ ላይ አዲስ ቀንን ከአዲስ ብርሃን ጋር ይዞ ከተፍ ይላል። የአጥቢያው ኮከብ፤ ለሚገፈፈው ጨለማ፤ ለምትመጣዋ ፀሐይ ማብሰሪያ ነው። የውበቱ ግርማ የቀኑን ብሩህነት ይነግረናል። አይታችን ሲጠነክር ከአንዱ ቦታ እየተወረወረ፤ ከሌላኛው ቦታ ላይ በኃይለኛ የብርሃን ምት ብው!" ሲል እናያለን። ከዘመናት በአንዱ ዘመን፤ ጥበብም እንዲህ ያለውን ልጅ ወለደች። ልጁም፤ በሙዚቃ ቤት አድጎ፤ ሙዚቃን ከልቡ ኖሮ ከልቡ ሠራት። የሙዚቃው የአጥቢያ ኮከብ፤ ኮሎኔል ሣሕሌ ደጋጎ ... ከስንት አንዱ እንደሚወረወሩቱ እንደ አጥቢያ ኮከቦቹ ሁሉ፤ እሱም ከስንት አንዴ ከሚፈጠሩ የጥበብ ከዋክብት መሐከል አንደኛው ነው።

ኮሎኔል ብሎ የጦር ሜዳ ጀግና እንጂ፤ የጥበብ አውድማ ልሂቅ አለ ለማለት ምናልባትም ለምናብ የሚከብድ ነው። ኮሎኔሉ ግን ጠመንጃን ፈቶ የመገጣጠም ያህል ሙዚቃንም እየፈቱ በልበ ሙሉነት ገጣጥመው ተዓምሩን ለማሳየት ችለዋል። ከጦር ሜዳው ጀብዱ ይልቅ፤ ከሙዚቃው መዋደዱ ልባቸውን እየፈነቀለ፤ "ላልከዳህ! ላልከዳሽ!" ተባብለው፤ በጥበብ ፊት ከሙዚቃ ጋር የቃለ መሐላውን የእምነት ማኅተብ አስረዋልና የቱ ጀግና፤ ማንስ ብርቱ ሊለያያቸው ... ለጥበብ መሰጠት ካሉ አይቀር እንዲህ ነው እንጂ።

እንደ ጥበብ አንቺ፤ እንደ ኪነ ጥበቡም አንተ፤ ስንል በፍቅር እንጂ ለአጥቢያ ኮከቡ የሚሆን ክብር ጠፍቶ አይደለም። ሥራው እንኳንስ እሱንና አንድ ፍሬ ጨቅላውንም "አንቱ" የሚያሰኝ ቢሆንም፤ የሙያ ልጆቹ ሁሉ "ጋሼ" ብለው አንተ፤ እንደሚሉት የአባት ፍቅር እጣን እንዲጤስ ነው። ኮሎኔል ጠመንጃ አቀባባይ፤ ዋሻ ሰርሳሪ ይሆናል ተብሎ ሲጠበቅ፤ ሙዚቃ ቀማሪ ሆኖ ቁጭ አለው። እሱ ሙዚቃን የወደዳትን ያህል፤ ጥበብም ከልጇ ሙዚቃ ጋር በፍቅር ወድቃለታለች። ጠላትን መማረክ ብቻም ሳይሆን፤ ጥበብንም በፍቅር፤ "ልብ ወደ ላይ!" ለማለት የቻለ ድንቅ የግጥምና ዜማ ደራሲ፤ የሙዚቃ መሣሪያዎች ተጫዋች ነበር።

ነጆ፤ ምዕራብ ወለጋ ይህን የዘመን ክስተት የሆነ የአጥቢያ ኮከብ አብቅላ ተመለከተች። ከተከበረው የባላንባራስ ደጋጎ ቤት ውስጥ ሣሕሌ ደጋጎ የተባለው ተዓምረኛ ልጅ ይወለድ ዘንድም ከላይ ተፈረደበት። ደጓ እናት ደጊቱ ፈይሳና ንጉሣዊው ባላንባራስ ደጋጎ አለቤ፤ በ1923ዓ.ም ሣሕሌ ደጋጎን፣ ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ዱብ አደረጉ። ይሰማኛል፤ የዚያን ዕለት...ከጎረቤታቸው ወይዘሮ ሱመያና ጋዲሴ፤ እንዲሁም ከአመለወርቅና ኤራዬ በላይ፤ የጥበብ የእልልታ ድምፅ እንዴት ሰፈሩን በአንድ እግሩ አቁሞ እንደነበረ።

ሣሕሌ ደጋጎ፤ አደገ ተመነደገ። ድክ ድክ ከማለት፤ ዱብ ዱብ ወደ ማለት ተሸጋገረ። አሁን ወሳኙ ነገር፤ ፊደል ቆጥሮ የቀለም ቀንድ ማብቀል ነበር። ይህን ቀንድ ፍለጋ ከነጆ ወደ ነቀምት አመራ። በዚያም የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቆ፤ ከሚንስትሪ ኩባያ ላይ የነበረችውን ጥያቄ ጭልጥ ቢያደርግም፤ በአንድ በኩል ብቻ ያለ ቀንድ ውበትንም ይገድፋልና ለሁለተኛው ቀንድ፤ አዲስ አበባ በመዝለቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ቀጠለ። ወደፊት ስሟን የሚያስጠራውን ጀግና የማስተማር ዕድሉን ለማሳለፍ አልፈቀደችምና፤ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት፤ እጇን ዘርግታ ተቀበለችው።

ልጅ በልጅነቱ የተመለከተውን ነገር፤ ቢረሳውም ልቡ ግን ፈጽሞ አይረሳውም። ገና ሕጻን ሳለ በባላንባራሱ፤ በአባቱ ዙሪያ ይመለከተው የነበረው፤ ጠመንጃና የወታደርነት መንፈስ፤ ደርሶ አሁን ልቡን ፈንቀል እያደረገ ይተነኩሰው ጀመር። ተማሪው ሣሕሌ ወታደር መሆን አማረው። ጠመንጃ ማንገብ፤ ለሀገር ቆሞ ለሀገር መዋደቅ፤ ልቡን ሰልቦ ምርኮኛ አደረገው። እናም፤ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀጥታ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር አመራ። እዚህስ ቢሆን ማንስ እጁን አጣመረበትና ... ደግሞ ከአንደኛ ክፍለ ጦር በ1942ዓ.ም ወደ ማዕከላዊ ዕዝ ተሸጋገረ፤ ወደ አንጋፋው የክቡር ዘበኛ ጦር ማለት ነው። ብቻ ይገርማል፤ ከነበረው ወታደራዊ ቅልጥፍናና ታዛዥነት የተነሳ፤ ከተራ ወታደርነት በአንድ ጊዜ የሃምሳ አለቅነት ማዕረግ፤ ከሳሪያን ኮቱ ላይ ተለጠፈለት። ሃምሳ አለቃ ሣሕሌ ደጋጎ።

ጥበብ ግን ይህንን ተመልክታም አልማረችውም። እጆችህ የሙዚቃ መሣሪያ እንጂ የጠመንጃ አይደሉም



ኮሎኔል ሣሕሌ ደጋጎ



አለች። ጣቶችህም ለፒያኖና ክላርኔት እንጂ ለቃታ አይደሉምና . . . በማለት፤ ምን ቀረ ሳትል፤ ይሄን የሙዚቃ መሣሪያ ባይነት ባይነቱ አስታቀፈችው። መሣሪያዎቹን በነካ ቁጥርም የሚፈሰው ግጥምና ዜማ ሆነ። ከሣሕሌ ጋር ትውውቅ ያደረገችው የመጀመሪያው የሙዚቃ መሣሪያ ክላርኔት ነበረች። አስቀድሞ በእግረኛ ባንድ ውስጥ ሳለ አሳምሮ ተጫውቷታል። እሷም ከእጁ ላይ ሆና ስትሽኮረመምና ትንፋሹ ከውስጧ ሲደባለቅ፤ አቤት! የምትሰጠው ድምፅ... በሣሕሌ ደቀመዝሙርነት ውስጥ፤ የሙሴ ኒኮ መምህርነት የሚረሳ አይደለም። ሙሴ ኒኮ፤ ፈረንሳዊ ምርጥ የሙዚቃ አስተማሪው ነው። ምናልባትም ከልጅነቱ የዳከረባቸውን ሁለቱን የእውቀት ቀንዶች፤ በክብር ያጠለቀለት ሰው ነው። የወይን ጣፋጭነት በፍሬው፤ እንዲሉ የሣሕሌ ጣፋጭነት በተነሳ ቁጥር፤ የዚህ ፈረንሳዊ ግንድነት አብሮ ይወሳል።

ወታደር ቤትና ሣሕሌ ደጋጎ፤ ማለትም አሁን ኮሎኔል እያልን ብንጠራው ይሻላልና ኮሎኔል ሣሕሌ ደጋጎ፤ እንደ እጅና ጓንት ልክክ አሉ። የክቡር ዘበኛ ኦርኬስትራ ባንድ ለእርሱ፤ እርሱም ለባንዱ ትክክለኛው ቦታና ምርጫ ነበሩ። ከነ ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ፣ ሻለቃ ግርማ፣ ባሻ ገብረአብ ተፈሪና ኮሎኔል ሣሕሌ በቤቱ ውስጥ የነበራቸው ጥምረት፤ የክቡር ዘበኛን ከማማው ላይ ሰቀለው። እዚህ ቤት ውስጥ ኮሎኔል ሣሕሌ ሙዚቀኛ ብቻ አልነበረም። እንደየቦታና አስፈላጊነቱ ረዥምና አጫጭር ድራማዎችንም እየጻፈ፤ ቤቱን በሁሉም አቅጣጫ ቀስቶ የያዘ ሁለገብ ቅስት ሆነ።

እሱ ማለት፤ ታሪካዊ ሥራዎቹን ከታሪክ ጋር ያዋሐደ፤ የጀግንነት መጠሪያው የማይበቃው ጀግና ቢሆንም፤ ሳይነገርለት የኖረና አንዳንዴም አሳዛኝ ነው። በወቅቱ ከነበሩትና ዛሬም ድረስ በልባችን ካዘልናቸው ድንቅ ድምፃዊያን፤ የኮሎኔሉን የግጥምና የዜማ ድርሰቶች እየጠረጠረ ያልበላ፤ እያዜመ ያላንቀረቀረ አለ ለማለት አይቻልም። ክቡር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ፤ ቀዳሚው ተጠቃሽ ነው። በትንሹ ሰባት ያህል የሙዚቃ ሥራዎች ላይ አብረው ማዕድ ቆርሰዋል። "ዋይ ዋይ ሲሉ" ልብን የሚሰብር፤ አሳዛኙ ገጽ ነው። ጊዜው በኢትዮጵያ ምድር፤ በኢትዮጵያ አድባር ላይ፤ ረሀብ ጸንቶ ዋይታና ሲቃው የበረታበት ጊዜ ነበር። ከዕለታት በአንዱ ቀን፤ የሙዚቃ ቡድን ኦርኬስትራው አባላትና ሌሎችም ለሥራ ወደ አሰብ በመሄድ ላይ ነበሩ።

በመኪናው መስታወት ወደ ውጭ የሚታየው ሁሉ ልብን ኩምሽሽ የሚያደርግና በኀዘን የሚደፍቅ ነበር። ከደረሱ በኋላ ወደ አንደኛው ወረዳ ጎራ ሲሉ፤ በዚያ ደግሞ ከብቱ ሁሉ አልቋል። ወንድ ልጅ የለም። ያለውም በረሀብ የፊጥኝ ታስሮና ተከዞ በሞት መስታወት ውስጥ እራሱን በመመልከት ላይ ነው። እጆቿ ቢቆረጡ በአፏ የምታጎርሰው እናት፤ ልጆቿን ከጅብና አሞራ ለማትረፍ አንዱን በጀርባዋ አዝላ፤ ሌላውን በቀኝና ግራ አቅፋ፤ በደረቷም ተሸክማ፤ ከሞት ሽሽት ትድሃለች። በስፍራው የተገኙትን አባላት የተመለከቱ ሕጻናት ልጆችም፤ ድንገት ሲሮጡ መጥተው ከዙሪያቸው ተኮለኮሉ።

"አባባ... ዋይ! ዋይ!...ግደሉን... ሞትን" በማለት ጠግቦ ባልተናገረው አንደበታቸው የሲቃ ድምጻቸውን በተማፅኖ ለማሰማት ሞከሩ። ኮሎኔል ሣሕሌ ሲያስታውሰውም፤ "ፍራንክ ብንሰጣቸውም ለልጆቹ ምንም አይጠቅማቸውም። እናም አሰብ ገባንና ሁለት ቀን ካደርን በኋላ፤ በሦስት ኩንታል ሞልተን ዳቦ ገዛንና ተመልሰን ወደ እዚያው ሄድን። ትንሽ እንኳን ሕይወት እንዲተርፍ በማሰብ፤ ለእያንዳንዱ አንዳንድ ድፎ ዳቦ ስናድል ዋልን።" ይላል፤ መጥፎውን አጋጣሚ ተንተርሶ የሠራትን ሙዚቃ፤ መነሻዋን ሲገልጽ። በሰዓቱ ጥበብ የከፈተችው የሣሕሌ የልብ በር ገርበብ እንኳን ለማለት አልቻለም ነበር። በመኪናው ውስጥ ሳሉም፤ በልጆቹ ዋይታ በልቡ እያነባ፤ "ዋይ ዋይ ሲሉ" የምትለዋን የሙዚቃ ግጥም በመጻፍ ላይ ነበር። "ዋይ እማማ፤ ዋይ አበባ ሲሉ፤ ሆዴ ባባ!" ይላል። አባላቱ ከአሰብ ተነስተው አዲስ አበባ ገቡ። እንዲህቹ ሲታገላት የደረሰው ይህ ሙዚቃም፤ ሁሉም ወደዱትና መሠራት አለበት በማለት ግፊት አደረጉ። "እንባው ከየት እንደመጣለት ባላውቅም፤ ጥላሁን ከልቡ እያለቀሰ ነበር የሠራው" አለ ኮሎኔል ሣሕሌ፤ በወቅቱ በድምፁ ያንቀረቀረውን የጥላሁን ገሠሠን ሁኔታ በማስታወስ።

**ዋይ ዋይ ዋይ ሲሉ፤**
**የረሀብን ጉንፋን ሲስሉ፤**
**እያዘንኩኝ ባይኔ አይቼ፤"**
**ምን ሳድርግ፤ አስፍኳቸው ትቼ ...**

አሳዛኙን ሀገራዊ ክስተት፤ ልብን ስንጥቅ በሚያደርጉ የግጥም ስንኞች፤ አንጀትን በሚበሉ የዜማ ፏፏቴዎች፤ አጥቦና ከሽኖ በድምፁ ቅላጼና ስርቅርቅታ መላ አካላትን ለሚቀሰቅሰው፤ ለሙዚቃው ንጉሥ ለጥላሁን ገሠሠ ሰጠው። ጥላሁንም፤ እንባውን ከአይኑ እያረገፈ፤ አድማጭ ተመልካቹን ሁሉ ከእንባ ዥረት እየቀዳ እንዲጠጣ አደረገው። የሁለቱ፤ በአንድ የሙዚቃ ማዕድ ዙሪያ ተቀምጦ መጎራረስ ተጀመረ እንጂ አላከተመም። "ስቆ መኖር" በሚለው ሥራቸው፤ ያለቀሰው ሁሉ ስቆበታል። ኮሎኔል ሣሕሌ በግጥምና ዜማው፤ ክቡር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ በድምፁ "እውነት ማሪኝ" አሉና ደግሞ እንደገና "ውሸት ለመናገር" በማለት "ልብሽን ለአፈርሰው"ን ደገሙት። ቢሆንም ግን "ይህቺ ጉብልማ መቅረት የለባትም ብለው በማሰብ፤ "ኮቱሜ" ሲሉ ትመጣ ዘንድ ጠሯት። የሁለቱ ጥምረትና ውሕደት ግን የሚጠገብ አልነበረም። አምጡት በላይ ላዩ፤ ስሩት በስር ስሩ ... የሚያስብልም ነበር። የሰሙበት ጆሮ እያጣጣመ ድገሙልኝ በማለት፤ ልብም ቅቤውን ጠጥቶ አልጠገብኩም ሲል እሰይ! እያለ አንጀትም ይርሳል።

የኮሎኔሉን አጥቢያ ኮከብነት፤ ጅምሩን እንጂ ፍጻሜው ድረስ ቆሞ አንድ ባንድ ለመመልከት ያዳግታል። ቃታውን እየሳበና ዒላማው ላይ እያነጣጠረ የሚያረግፈውን የሙዚቃ እንኮይ፤ እስኪጠግቡ ይበሉት ይሆናል እንጂ ቅርጫት ሞልቶ ለመሸከም የማይቻል ነው። እጅግ ግሩም በሆነ መልኩ፤ ይህ ድንቅ ኮሎኔል አራት መቶ (400) ያህል የሙዚቃ እንኮይ በማርገፍ፤ የሙዚቃ አድማጩን ረሀብ ወደ ጥጋብ ለውጦታል። ምን ይሄ ብቻ፤ አንድ መቶ ያህል የኦሮምኛ ሙዚቃዎችንም በመሥራት፤ ሁለገብነቱን ብቻም ሳይሆን ሁሉ አዋቂነቱንም አስመስክሯል። አዋቂ ክፉ አይወጣውምና "አይወጣኝም ክፉ ነገር" ሲል በብዙነሽ በቀለ ሙዚቃ ውስጥ ነገረን። "ከንቱ ሥጋ"፤ "አታሳየኝ ጭንቁን"፤ "የፍቅር ወጋገን"፤ "ቃልኪዳን"፤ "ፍቅርህ ቀሰቀሰኝ" እና ሌሎችንም ግጥምና ዜማዎችን በመሥራት፤ ለብዙነሽ በቀለ ሰጥቷል። ድምፃዊቷ መንበረ በየነ "እንዴት ከረማችሁ" ስትል፤ ግጥምና ዜማው በኮሎኔሉ ነው።

የኮሎኔል ሣሕሌ ደጋጎ ሌላኛው ምትሐታዊ ብቃት፤ ግጥምና ዜማ ከመሥራትና የሙዚቃ መሣሪያዎቹን እንዳሻው ከማናዘዝ ያለፈ ነው። በአንድ ሙዚቃ ሙሉዕነት ውስጥ የቀረው ነገር ግጥምና ዜማውን አዋዶ ሙዚቃ ማቀናበር ነበር፤ ጥበብ እሱንም አንስታ ሰጠችው። የጥበብ ለጋስነት፤ የእርሱም የታማኝነት ልክ ምትሐት ነው። ጥበብ ፍሬዋን የዘራችው፤ ከትክክለኛው ለም መሬት ላይ ነበርና፤ አንዱ ሃምሳና ስድሳ ... መቶና አራት መቶ፤ አልፎም አምስት መቶ አፈራ። ታዲያ ይህ ምትሐት አይደለምን?

**ወደ መጣሁበት ምድር፣**
**እስከመለስባት በክብር፤**
**ሰውን ከማስደሰት በቀር፣**
**አይወጣኝም ክፉ ነገር።**

ቀደም ሲል ያነሳነውን "አይወጣኝም ክፉ ነገር" የተሰኘውን፣ ይህን የብዙነሽ በቀለን ጥዑም ዜማ፤ በፍቅር እስክንወድቅበት ድረስ አሳምሮ ያቀናበረው ይሄው ኮሎኔል ሣሕሌ ነው። "ፍላጎቴ"፤ "ምን ነበር"፤ "ምንድን ነው ትዝታህ" የሚሉት ሥራዎቿንም እንዲሁ በቅንብር ያዋሓዳቸው እርሱ ነው። "ይህ ነው ጌትነት" እና "የምድር ፈተና" የተሰኙትን ጨምሮ በ1966 ዓ.ም፤ በውብሻው ስለሺ የተዜሙትን ተወዳጅ ሥራዎች አቀናብሮ ለክብር አብቅቷቸዋል። የተፈራ ካሣን "የከተማው"፤ "ሥራ ፈቶ ሲያይሽ"፤ እንዲሁም፣ "መጠን አትለፉ" የሚሉ ጣፋጭ ሙዚቃዎችን ስናደምጥ፤ ኮሎኔል ሣሕሌም ከጀርባ አለበት።

**በመጠጥ ደስታ ይገኛል ብላችሁ፤**
**መጠን አትለፉ ትቃጠላላችሁ፤**

ስንቱ በማንኪያ የማይሞላለትን፤ እርሱ በጭልፋ ከዛቀው፤ ስንቱን ጨልፈን እንደምንችለው ግራ ነውና እነኚህን ሥራዎቹን እንጨምር። "በመጠጥ ደስታ"፤ "አላዝንም ለራሴ"፤ "አሸብርቆ ደምቆ" "ከረሜላ ነህ" እና በሌሎችም የልዩ ልዩ ድምፃውያን ሥራ ላይ ከግጥምና ዜማ እስከ ቅንብር ተሳትፎባቸዋል። በሙዚቃው አድማስ፤ ከግጥምና ዜማው እስከ ቅንብር ውሕደቱ ድረስ፤ ከማሕሙድ አሕመድ አንስቶ ጥሶ ያልገባበት የግዛት ድንበር የለም። የአጥቢያ ኮከብ ነውና ደምቆ በብርሃን ሊታይበት የማይችልበት ወሰን የለም።

ኮሎኔል ሣሕሌ ደጋጎንማ ጥበብ እራሷ በሰማይ ውለታውን ከፍላ ታስተሰርየን እንጂ፤ እንደኛማ ውለታ መላሽነት ... ቀና ብለን በሁለት ዓይን ለማየት አያስደፍረንም። ኮሎኔሉ በእድሜ ዘመኑ "ተበርክቶለታል" ተብሎ የሚነገርለት ይህ ነው። በአንድ ወቅት የክብር ሜዳሊያና የ20ሺህ ብር የገንዘብ ስጦታ፤ በረዥም ዓመታት ውስጥ፤ በ10፣ በ20 እና 30 ዓመት ለእያንዳንዱ ከወርቅ እስከ ነሐስ ተበርክቶለታል። በ1991 ዓ.ም ደግሞ የሕይወት ዘመን ሽልማት አግኝቷል። ለተዋጊ ወታደርነቱ ደግሞ የደረት ላይ ዓርማ የሆነውን ኒሻን ተሸልሟል።

በአንድ ወቅት፣ የሙዚቃ ቀማሪው፤ የግጥምና ዜማው ጌታው ኮሎኔል ሣሕሌ ደጋጎ በጠና ታመመ። ለስንቱ ደርሶ ስንቱን እንዳልሠራ፤ የዚህን ጊዜ ግን ሕክምናውን እንኳን በቅጡ ለመከታተል ሳይችል ቀረ። እጅግ አዝኖና ተከዞ የሞትን የጥሪ ድምፅ መጠባበቅ ጀመረ። የእርሱን ሕይወት ለእናት ሀገሩና ለጥበብ ሰጥቶ የኖረው ሰው፤ "እንዴትስ የሚያሳክመኝ ልጣ? ብሎ፤ ማንንስ ይውቀስ? የነበረው አማራጭ በኀዘን እየተብሰለሰሉ ዝም ማለት ነበር። ይህን የሰማችው እውቋ ጋዜጠኛ ስንዱ አበበም ልታወጋው ስትገሰግስ ከቤቱ ደረሰች። እሱ ግን በመታመምና በመከፋት ጥምልምል ብሎ፤ በተስፋ መቁረጥ ተሸብቦ ነበር የደረሰችው። እናም፣ በጨዋታቸው መሐል፣ "እኔ ለአለቤ ሾው አንሳለሁ?" የሚል፤ ብስጭት አዘል የብሶት ጥያቄ ጠየቃት። "አለቤ ሾው" በወቅቱ ሕዝቡ ሁሉ በፍቅር የተማረከለት የቴሌቪዥን ዝግጅት ነበርና ወዲህ ጎራ ብሎ ችግሩን መናዘዝ ለቻለ፤ ጧሪ ደጋፊው ብዙ ነው።

የተሸከመውን ቀንበር ለመቋቋም የተሳነው ኮሎኔል ሣሕሌም፣ በዚህ ቀርቤ ችግሬን ለኖርኩለት ሕዝቤ ላጋራ በማለት፤ የአዘጋጁን የአለባቸው ተካን ደጅ ጠንቶ፣ አለቤ ግን ለካስ በጊዜው ሳይደርስለት ኖሯል፣ "እኔ ለአለቤ ሾው አንሳለሁ?" ብሎ ንድድ ማለቱ ለዚሁ ነበር። ይህ ለዛሬው ሚዲያዎቻችንም ጭምር የሚሆን ጥያቄና የሕሊና እዳ ነው። አለቤ በመጨረሻም ቢሆን፤ ደርሶ ክሶታል። ያማረ ቆይታ በማድረግም ሕክምናውን እንዲያገኝ አደረገው። ሞት ግን መካሪ የለውምና ቋምጦ እንደተመኘውም፣ መጋቢት 6 ቀን 2002 ዓ.ም ላይ አገኘውና ይዞት ከነፈ። ተላላው ሞት፤ ኮሎኔል ሣሕሌን ያህል ሰው ይሞት መስሎሃል ... ይህ አይነቱ የአጥቢያ ኮከብነት፤ ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም!!!

# ዓለም አቀፍ

## ብሊንከን ሩስያ በዩክሬን ላይ እየፈጸመችው ላለው ጥቃት ቻይና ድጋፍ እንዳታቀርብ ጠየቁ

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ሩስያ በዩክሬን ላይ እየፈጸመችው ላለው ጥቃት እያቀረበች ካለችው ድጋፍ ቻይና እንድትቆጠብ አስጠነቀቁ።ቻይና ለጥቃቱ የሚሆኑ ቁሶችን እያቀረበች ነው ሲሉ የወነጀሉት ብሊንከን፣ይህንን ካላቆመች ሀገራቸው እርምጃ እንደምትወስድ አስጠንቅቀዋል።

ቻይና ከቀዝቃዛው ጦርነት ወዲህ "በአውሮፓ ደኅንነት ላይ የተጋረጠውን ስጋት እያቀጣጠለች እና እየረዳች" መሆኑን በቤጂንግ በነበራቸው ቆይታ ከባለስልጣናቱ ጋር መነጋገራቸውን ብሊንከን ገልጸዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሀገራቸው በቻይና ላይ እርምጃ እንደምትወስድ ቢናገሩም ምን እንደሆነ ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ተቆጥበዋል።

ብሊንከን በቤይጂንግ ቆይታቸው በአንዳንድ ሁኔታዎች መሻሻል መታየቱን ጠቅሰው፤ ለዚህ ዋቢ ያደረጉትን ፌንታኒል የተሰኘው አደንዛዥ እፅ ወደ አሜሪካ እንዳይደርስ ለማስቆም ባለስልጣናቱ ያደረጉትን ጥረት አወድሰዋል። በመላው አሜሪካ የሕዝብ ጤና ቀውስ እየፈጠረ እንደሆነ በዋይት ሃውስ የተነገረለት ፌንታኒል አደንዛዥ እፅ ዋነኛ ምንጩም ቻይና መሆኗ ይነገራል።

ብሊንከን በተጨማሪ ቻይና ከኢራን ጋር ያላትን ግንኙነት በመጠቀም ከእስራኤል ጋር ያለው ጦርነት የበለጠ እንዳይሰፋ በማድረግ ረገድ በመካከለኛው ምሥራቅ "ገንቢ ሚና" መጫወት እንደምትችል አጽንዖት ሰጥተዋል። በአስር ወራት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ይህ ጉብኝታቸው በሁለቱ ተቀናቃኝ ኃያል ሀገራት መካከል ያለውን ውጥረት በማርገብ ወደ ዲፕሎማሲ እና ውይይት ለማምጣት የሚያደርጉት ጥረት አካል ነው ተብሏል።

በሁለቱ ሀገራት መካከል ዋነኛ ውጥረት መነሻ ሆኖ የቆየው ቻይና ታይዋንን እንደ አንድ ግዛቷ መመልከቷ ሲሆን፤ በቅርቡ አሜሪካ ለታይዋን ካካሄደችው የጦር



አንቶኒ ብሊንከን ሩስያ

መሳሪያ ሽያጭ ጋር በተያያዘ በአምስት የምዕራባውያን የመከላከያ ድርጅቶች ላይ ማዕቀብ እንደምትጥል ቻይና ማስታወቋ ይታወሳል። እንዲሁም ባለፈው ዓመት አሜሪካ ቻይና የላከችው የስለላ ፊኛ ነው በሚል መትታ መጣሏን ተከትሎ የሀገራቱ ውጥረት ተጋግሎ ነበር።

በቅርብ ቀናት ውስጥ ደግሞ ባለቤትነቱ የቻይና የሆነው የቪዲዮ መተግበሪያ ቲክቶክ በአሜሪካ ያለው ድርሻ እንዲሸጥ ወይም እንዲታገድ የሚያስገድድ ሕግ ፓርላማው አውጥቷል። ብሊንከን ከቻይናው ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ ጋር በነበራቸው ውይይት የቲክቶክ ጉዳይ እንዳልተነሳ ገልጸዋል። ፕሬዚዳንት ጂንፒንግ በበኩላቸው በኅዳር ወር ከአሜሪካ አቻቸው ጆ ባይደን ጋር ከተገናኙ በኋላ በሁለቱ ሀገራት መካከል "አንዳንድ አዎንታዊ መሻሻል አሳይተዋል" ብለዋል።

አሜሪካ ለቻይና ዕድገት አዎንታዊ አመለካከት ማሳየት ከቻለች የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት "ሊረጋጋ፣ ሊሻሻል እና ወደፊት ሊራመዱ ይችላሉ" ያሉት ፕሬዚዳንት ጂንፒንግ "ተፎካካሪዎች ሳይሆኑ አጋር መሆን አለባቸው" ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## የሀውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባህር በነዳጅ ጫኝ መርከብ ላይ ጥቃት አደረሱ

የሀውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባህር በነዳጅ ጫኝ መርከብ ላይ ጥቃት ማድረሳቸው ተገለጸ። የሀውቲ ታጣቂዎች ባስወነጨፉት የባለስቲክ ሚሳይል የፓናማ ሰንደቅ አላማ እያውለበለች በቀይ ባህር ስትጓዝ በነበረች ነዳጅ ጫኝ መርከብ ላይ አነስተኛ ጉዳት ማድረሱን ባለስልጣናት ተናግረዋል።

የሀውቲ ታጣቂዎች ከጋዛ ጦርነት ጋር በተያያዘ በቀይ ባህር በሚንቀሳቀሱ መርከቦች ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት ለአንድ ወር ያህል ጋብ ካደረጉ በኋላ ይህን ጥቃት ፈጽመዋል። ታጣቂዎቹ ካስወነጨፏቸው ሦስት ሚሳይሎች ውስጥ አንዱ በሲሸልስ በተመዘገበችው እና የፓናማ ሰንደቅ አላማ ስታውለበልብ በነበረችው 'አንድሮሜዳ ስታር' ላይ ጉዳት እንዳደረሰባት የአሜሪካ ጦር ማዕከላዊ ኮማንድ ገልጿል።

የግል የጸጥታ ኩባንያው የሆነው አምብሬይ እንዳለው መርከቧ ከሩሲያ ጋር ግንኙነት ባለው ንግድ የተሰማራች ነች። ኩባንያው እንደገለጸው፤ ከሆነ መርከቧ ከሩሲያ ፕሪሞርስክ ተነስታ ወደ ቫዲናር ህንድ በማቅናት ላይ ነበረች ብሏል። የሀውቲ ታጣቂዎች ቃል አቀባይ ብርጋዴር ጀነራል ያህያ ሳሬ ባወጣው ቀድሞ ሪከርድ በተደረገ ቪዲዮ መግለጫ ለጥቃቱ ኃላፊነት ወስዷል።

ቃል አቀባዩ እንዳሉት፤ መርከቧ ኢላማውን የጠበቀ ምት አርፎባታል። ጥቃቱ በተፈጸመበት ወቅት የባርባዶስ ሰንደቅ አላማ ስታውለበልብ የነበረች ሌላ መርከብ በቅርብ ርቀት ላይ እንደነበረች አሜሪካ ገልጻለች። ይህ ጥቃት የተፈጸመው ቀይ ባህር እና የኤደን ባህረ ሰላጤ በሚገናኙበት የባብኤል ማንዴብ የባህር ወሽመጥ አቅራቢያ ነው።

የሀውቲ ታጣቂዎች ከእስራኤል ጋር እየተዋጋ ላለው የፍልስጤሙ ታጣቂ ሀማስ አጋርነት ለማሳየት ነበር ከባለፈው ህዳር ወር ጀምሮ ከእስራኤል ጋር ግንኙነት ያላቸውን መርከቦች እንደሚያጠቁ ያሳወቁት። እንደ አሜሪካ ማሪን አድሚኒስትሬሽን ከሆነ የሀውቲ ታጣቂዎች ከባለፈው ህዳር ወር ጀምሮ በመርከቦች ላይ 50 ጥቃቶችን ሰንዝረዋል። ታጣቂዎቹ አንድ መርከብ የያዙ ሲሆን፤ ሌላ አንድ መርከብ ላይ ደግሞ ጉዳት በማድረስ እንድትሰጥም ማድረጋቸውን አል ዐይን ዘግቧል።





### ማስታወቂያ

ፋሲካ ተረፈ ወ/ማርያም በአዳማ ከተማ አስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር WPKMB/173/14 በ27/11/2014 በተጻፈ ከጤና ጥበቃ በጁኒየር አሲስታንት ክሊኒካል ነርስ(Junior Assistant Clinical Nurse) በመዝገብ ቁጥር/ACN=276/96-RPL=12 በ22/1/97 ዓ.ም የወሰዱት የምሥክር ወረቀት የጠፋ መሆኑን አሳውቆናል፡፡
ስለዚህ የባለሙያውን የሙያ እና የሥራ ፍቃድ ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት አግኝቼዋለሁ በእዳ ይገቼዋለሁ የሚል ተቃዋሚ ካለ እስከ 15 ቀን ድረስ ይዞ ይቅረብ ባይቀርብ በምትኩ ተለዋጭ የምስክር ወረቀት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የኦሮሚያ ጤና ጥበቃ ቢሮ**

### ማስታወቂያ

አቶ አብደላ ኡስማኤል ኢረና በ2oo8 ዓ.ም. ከጅማ ዩኒቨርሲቲ በ Animal Health የትምህርት መስክ የተመረቁበት ቴምፖረሪ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ ስለጠፋባቸው ወድቆ አግኝቻለሁ የሚል ቢኖር ወይም በማንኛውም ምክንያት የያዘ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ካልቀረበ በምትኩ የሚሰጣቸው መሆኑን እናስታውቃለን ፡፡

**የጅማ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ጽ/ቤት**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦራ ወረዳ ቦቴ ከተማ በ0026690842 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ቦቴ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በግብር/ታክስ ከፋይነት ክተመዘገብኩበት ከኢፌዴሪ ገቢዎች ሚኒስቴር አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህትመት ፈቃድ በማግኘት ከምንጠቀምባቸው የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ተ/ቁጥር 3801-3850 እና 4151-4200 ያልተሰራበት ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ (2 ፓድ) እንዲሁም ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ግብር የሚሰበሰብበት ደረሰኝ (ዊዝሆልዲንግ) ከቁጥር 0001- 0050 ድረስ የተሰራት በ(1 ፓድ) ስለጠፋብኝ በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸሙ በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው ከኢፌዴሪ ገቢዎች ሚኒስቴር አዳማ ቅርንጫፍ የቤት ወይም በአቅራቢው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርጉልን አስታውቃለሁ፡፡

**ቦቴ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት እነ ወ/ሪት አይዳ ፍቅረማርያም እና የፍ/ባለዕዳ አቶ ደምሰው ፍቅረማርያም መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/93449 በ25/4/2016 ዓ/ም እና በኮ/መ/ቁ/96888 በ19/5/2016 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 177 የሴርያል ቁጥር R055152 የሆነ በካ/ቁ// በይዞታ መለያ ኮድAA000100803848 የተመዘገበ ካርታ ያለው የይዞታው ስፋት በካርታቸው መሰረት 226.18 ካ/ሜ ይዞታውን 2.4 ካ/ሜ መንገድ ይነካዋል የቤቱ አዋሳኞች በሰሜን ባዶ ቦታ ፤በደቡብ ቤዛዊት በድሩ በምስራቅ መንገድ እና በምዕራብ ባዶ ቦታ የሐራጅ መነሻ ዋጋ ብር 14,908,103.10(አስራ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሶስት ብር 10/100) ሆኖ የትራዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ግንቦት 22 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ 8፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባበት ቦታ ድረስ በመውሰድ ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ c.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚያመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አፈ/ዳ/ ስም c.P.O በኢትዮያ ንግድ ባንክ ብቻ አሰርቶ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ የፍ/አፈ/ዳይሮክቶሬቱ ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሐራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

# ስፖርት



## ፓሪስ እና ስፖርት

ብርሃን ፈይሳ

የፍቅር፣ የሥነጥበብ፣ የፋሽን፣... ከተማዋ ፓሪስ ከስፖርትም ጋር በእጅጉ የተወዳጀች ነች፡፡ በአውሮፓ ስመጥርና በኀብኘዎች ዘንድ ተዘውታሪ ከሆኑ ከተሞች መካከል አንዷ የሆነችው ፓሪስ፤ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ በጉጉት የሚጠበቁ ታላላቅ ስፖርታዊ ውድድሮችን በማስተናገድም የተመሰከረላት ናት። የስፖርቱ ዓለም ቁጥር አንድ የሆነውን ስፖርታዊ ውድድር ኦሊምፒክንም በታሪኳ ለሦስተኛ ጊዜ ለማሰናዳት 95 ቀናት ብቻ ቀርተዋታል፡፡

በርካታ ታላላቅ ስፖርታዊ ውድድሮችን ለማሰናዳት ተመራጭ ከሆኑ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ስፖርት ዓይነቶች ምቹ የሆኑ ማዕከላት ካሏቸው ቀዳሚ 10 ከተሞች መካከል አንዷ የፈረንሳዊያን ኩራት የሆነችው ፓሪስ ናት፡፡ ከተማዋ ብቻም ሳትሆን እንደአጠቃላይ ፈረንሳይ ታላላቅና እጅግ ዘመናዊ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን መገንባትና ውድድሮችንም መሳብ የቻለች ከተማ ናት። የዓለም ሻምፒዮናው የእግር ኳስ ቡድኗ እንዲሁም የእግር ካስ ሊጓ በአውሮፓ ታዋቂ ከሆኑት መካከል የሚመደብ እንደመሆኑ ከስፖርቱ ጋር ጠንካራ ቁርኝት አላት፡፡ ከአትሌቲክስ ስፖርት ጋርም ስሟ በስፋት የሚያያዘው ከተማዋ ዓመታዊው ፓሪስ ማራቶን ከመለያዎቿ መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ ዝነኛ አትሌቶችን ጨምሮ በርካቶችን የሚያሳትፈው ይህ የጎዳና ላይ ሩጫ ከኒው ዮርክ ማራቶን ቀጥሎ ሁለተኛው የዓለም ትልቁ ሩጫ ነው፡፡

ታላቁን የብስክሌት ውድድር ቱር ደ ፍራንስን ጨምሮ የኦሊምፒክ ደረጃን የሚያሟሉ በርካታ የዋና ገንዳዎቿ፣ የሜዳ ቴኒስ፣ የፈረስ ግልቢያ፣ የራግቢ እና ሌሎች ስፖርታዊ ውድድሮች በፓሪስ አፈር ላይ ከ‹‹ኤፍል›› ማማ ስር የሚከወኑ ታላላቅ ሁነቶች ናቸው። አሁን ደግሞ ኦሊምፒክን ለማስተናገድ ሽር ጉዷን እያጠናቀቀች ትገኛለች፡፡ በእርግጥም ፈረንሳይና ፓሪስ ስፖርታዊ ሁነቶችን በማካሄድ ብቻም ሳይሆን ለዓለም የስፖርት ታሪክ ስማቸው ለዘመናት ሲወሳ የሚኖር ታላቅ ባለሙያዎችንም አፍርታለች፡፡ በተለይ የዘመናዊው ኦሊምፒክ ምስረታ ሲታሰብ የጥንስሱ ባለቤት የሆኑት የስፖርት እና የሥነጥበብ ሰው እንዲሁም መምህሩ ፒየር ደ ኩበርቲን አብረው ይነሳሉ። ጥንታዊው የአቴናውያን ልማድና የአምልኮ ሥርዓት የሆነው ኦሊምፒክ ከዘመናት በኋላ በዘመናዊ መልክ ተቃኝቶ የዓለምን ሕዝብ የሚያስተሳስርና ሠላምን የሚሰብክ እንዲሆን ያደረጉት ፈረንሳዊው የስፖርት አባት ናቸው፡፡



እአአ በ1896 የኦሊምፒክ ትውልድ ሃገር የሆነችው ግሪክ የመጀመሪያውን ዘመናዊ ኦሊምፒክ አቴንስ አስተናገደች፡፡ ከአራት ዓመት በኋላ ተራው የፓሪስ በመሆኑ ከተማዋ ከግሪክ ውጪ ኦሊምፒክን ያስተናገደች የዓለም ቀዳማዊቷ ከተማ በመሆን በማጎደሯ ሌላኛውን ታሪኳን ልትመዘግብ ችላለች፡፡ የከተማዋ ቀጣዩን ኦሊምፒክ ለማስተናገድ 24 ዓመታትን ብቻ የጠበቀች ሲሆን፤ አንደኛው የዓለም ጦርነት ከተጠናቀቀ በኋላ የተካሄደ ሁለተኛው ኦሊምፒክ መሆኑንም ታሪክ ያወሳል፡፡ በወቅቱ የዘመናዊው ኦሊምፒክ መሥራችና የዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት የሆኑት ፒየር ደ ኩበርቲን የመጨረሻው ቆይታ በመሆኑም ታሪካዊ ያደርገዋል፡፡

ኦሊምፒኩ ከ44 ሃገራት የተወጣጡ 3ሺ የሚሆኑ ስፖርተኞች ተሳታፊ የነበሩበት ሲሆን፤ የመክፈቻ እና መዝጊያ መርሐ ግብሮቹን በኮሎምበስ ስታዲየም በማድረግ ነበር የተካሄደው፡፡ ወቅቱ ፓሪስ የመጀመሪያውን የኦሊምፒክ የዋና ገንዳ፣ የኦሊምፒክን መንደር ያስተዋወቀችበት እንዲሁም ጥቂት ስፖርቶች ላይ ለውጥ የታየበትም ነበር፡፡ በጥንታዊ ነገር ግን አስደናቂ በሆኑ ኪነ ሕንጻዎቿ የምትታወቀው ተወዳጇ ከተማ ፓሪስ ሦስተኛውን ኦሊምፒክ ለማካሄድ 100 ዓመታትን ጠብቃለች፡፡ ይህም ታሪካዊ ሊባል የሚችል ጉዳይ ሲሆን፤ ይህንን ተከትሎም በኦሊምፒክ ባሕል መሠረት ከተለመደው ውጪ የመክፈቻ እና የመዝጊያ መርሐ ግብሮቹ በስታዲየም ውስጥ አይደረጉም፡፡

ይህ ኦሊምፒክ ታሪካዊ ሊያስብለው የቻለው ፓሪስ ለአዘጋጅነቷ አንድ ክፍለ ዘመን ያስቆጠረችበት ብቻም ሳይሆን ከሴቶች ተሳትፎ ጋር በተያያዘም ነው፡ እአአ በ1924 ፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ ከተካፈሉ 3ሺ አትሌቶች መካከል የሴቶቹ ቁጥር 100 ብቻ ነበር። በኦሊምፒክ ኮሚቴው በኩል ተሳትፎው በየጊዜው እያደገ ነው ይባል እንጂ የሚፈለገውን ግብ ሳይመታ ዘመናትን ማስቆጠሩ አልቀረም፡፡ ከሦስት ወራት በኋላ በሚደረገው 33ኛው የፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ ግን እኩል የተሳትፎ ታሪክ እንደሚመዘገብ ከወዲሁ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡




## አይጥና አንበሳ!

እዮሩስ ተስፋዬ

ሠላም፣ ጤና እና መልካም ነገሮችን ሁሉ የምንመኝላችሁ ውድ ልጆቻችን እንዴት ናችሁ? ሳምንቱ እንዴት አለፈ? እንደሚጠበቀው በጥናት እና በትምህርት በሚገባ አሳልፋችኋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ልጆችዬ ወላጆቻችሁ ወይም መምህራን ‹‹አባባ ተስፋዬ›› ሲሉ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? በእርግጥ ዛሬ በሕይወት ባይኖሩም ብዙዎች ‹‹ልጆች የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች›› በሚል ንግግራቸው እንዲሁም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ‹‹የልጆች ክፍለ ጊዜ›› በተሰኘው ፕሮግራም ለልጆች በሚያቀርቡት ታሪክ ያስታውሷቸዋል።

‹‹አባባ ተስፋዬ›› ሙሉ ስማቸው ተስፋዬ ሣሕሉ ይባላሉ። በ1978 ዓ.ም ‹‹ከአባቶች ለልጆች›› የተሰኘ ሦስተኛ መጽሐፋቸውን አሳትመው ነበር። በዚህ የተረት መጽሐፍ ‹አንበሳና አይጥ› በሚል ርዕስ የቀረበውን አንድ አስተማሪ ታሪክ እናቀርብላችኋለን። ታሪኩ እንዲህ ይጀምራል፤

አንድ ጊዜ አንበሳ ምግቡን ለማግኘት አጋዘን ሲያባርር ውሎ ከያዛት በኋላ ምግቡን በልቶ የቀረበውን በአንድ ስፍራ አስቀምጦ ተመልሶ በጣም ስለደከመው ጋደም ብሎ ተኝቶ ነበር። ግን እንቅልፍ አልወሰደውም። በዚህ መሐል አንድ አይጥ ምግቧን ፍለጋ ከወዲያ ወዲህ ስትራወጥ ሳለ አንበሳ ከተኛበት ስፍራ ትደርስና ዙሪያውን ትዞራለች። አይንቀሳቀስም። አሁንም በሰውነቱ ላይ ታልፋለች አይንቀሳቀስም። አሁን በመዝናናት ቀስ ብላ እራሱ ላይ ትወጣና ከጆሮው ግድም ለመብላት ስትሞክር ጆሮውን ነቅነቅ ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ዘላ ትወርድና መንቃነቁን ስላልደገመ ወደ አፍንጫው ተጠግታ መተንፈሱን አዳመጠች፤ እሱ ግን አፉን ከፍቶ ልክ እንደሞተ ሆኖ ተኝቶ ስለነበር አንዴ ባፉ ውስጥ አለፈችና ሁለተኛ ስትገባ ጥርሱን ግጥም አድርጎ ያዛትና ‹‹ለምን መኝታ ከለከልሽኝ፤ አሁን ዋጥ ላድርግሽ?›› ቢላት ደንግጣ ‹‹አያ አንበሳ አትዋጠኝ። የዛሬን ማረኝ። ዛሬ ብትምረኝ እኔ ደግሞ ላንተ አንድ ቀን ውለታ እመልሳለሁና ማረኝ?›› አለችው።

አንበሳው ከት ብሎ ሳቀና ‹‹የሚያስቀሳፍትሽ (የሚያስቀባጥርሽ) የነፍስ ሲቃ ይዞሽ ነው እንጂ አንቺ ለእኔ ብድር መላሽ ልትሆኚ አትችይም፤ ይልቅ ማረኝ በይና ልልቀቅሽ?›› አላትና ለቀቃት።

አይጥ ግን ስለለቀቅሽኝ ‹‹በጣም አመሰግንሀለሁ። ብድርህን ለመመለስ ያብቃኝ›› ብላው ሄደች።

በዚህ ሁኔታ ከቆዩ በኋላ አዳኞች ወጥመድ አጥምደው ኖሮ አንበሳ እዛ ወጥመድ ውስጥ ገብቶ ለመውጣት ሲታገል አይጥ ምግቧን ፈልጋ በዛ ስታልፍ ድንገት አንበሳ ተይዞ ታየውና ‹‹አያ አንበሶ ምን ሆነህ ነው በዚህ ግድም የተገኘሽው?› ብላ ጠየቀችው።

አንበሳም ‹‹ይሔው እንደምታይኝ እዚህ ወጥመድ ውስጥ ገብቼ እጨነቃለሁ።›› አላት። አይጧም ‹‹ወጥመድን ያጠመዱ ሰዎች ድንኳናቸው ውስጥ ምሳቸውን ሲበሉ ነበር። ከመምጣታቸው በፊት እንዳወጣህ ስለምፈልግ አይዞህ! ጓደኞቼን ይገቬ ልምጣ?›› ብላ ካጠገቡ ፈትለክ በማለት እየሮጠች ሄደች።

አንበሳም ‹‹አይ አትልፊ አሁን ያንቺን ጉልበትና የጓደኞችሽን ጉልበት እኔን ከዚህ ውስጥ ሊያወጣኝ ነው? ይልቅ ተይው ፤ አልኩ ለማለት እንደሆነ ሃሳብሽ ይበቃል።›› አላት።

አይጥ ግን ‹‹ግዴለም›› ብላ ጓደኞቿን አንድ አይጥ ሳይቀር ይዛ ከተፍ አለችና ያ ወጥመድ የታሰረበትን ጠፍርና ገመዱን ብጥስጥሱን ካወጡት በኋላ ‹‹በል አሁን በኃይል ተወራጭ በዛን ጊዜ ግንዱ ሁሉ ይንከባለላል።›› አለችና ነገረችው።

አንበሳም ‹‹አይ አይጢት ስንቴ ሞክሬው ያልሆነውን?›› ብሎ በትክክሻው ገፋ ቢያደርገው ያ ግንድ ሁሉ ተንከባለለ። አንበሳ ከወጥመዱ ውስጥ ወጣ።

አይጢት ‹‹በል ሂድ እኔም ቃሌን ፈጽሜያለሁ። አንድ ቀን ብድር እመልሳለሁ ብዬ ነበር ያው አንተ ስለማርከኝ ብድሬን መልሻለሁ። አንተ ግን ትንሽ ነች ብለህ ንቀኸኝ ነበር።›› ካለችው በኋላ ‹‹ሳይመጡብህ አምልጥ።››ብላ እሷም ከነጓደኞቿ ወደ ጉድጓዷ ገባች ይባላል።

‹‹ልጆች ሰውንም ሆነ እንስሳን ትንሽ ነው ብለው መናቅ አይገባም። ሰውም ለጭንቅ ቀን ይገኛል። ትንሽ አውሬም ሰውን ያበላሻልና።›› በማለት አባባ ተስፋዬ መልካሙን ምክራቸውን በመጽሐፋቸው ላይ አቅርበዋል።

ልጆችዬ ከአይጢቷ እና ከአያ አንበሳ ታሪክ ቃል ማክበር እንደሚገባ፣ አጉል ድፍረት እንደማያስፈልግ ፣ትንሽ ናት ወይም ነው ብሎ ማንንም መናቅ እንደማይገባ፣ በመተባበር እና በመረዳዳት እንዴት ከችግር መውጣት እንደሚቻል ከዚህ ታሪክ እንደተማራችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። በተረፈ ደግሞ እናንተ የተማራችሁትን እንዲሁም ያገኛችሁትን እውቀት ለታናናሾቻችሁ እና ለጓደኞቻችሁ በማካፈል መልካም ነገር እንዲማሩ ለማድረግ እንደምትጥሩ ተስፋ አደርጋለሁ። ልጆችዬ ለዛሬ በዚሁ እናብቃ ሳምንት በሠላም ለመገናኘት ያብቃን።